# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ዓርብ

82ኛ ዓመት ቁጥር 167 የካቲት 17 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









# በቦረና ዞን በተከሰተው ድርቅ ከ800 ሺህ በላይ ሰዎች ተጎጂ ሆነዋል

- ሁለት ሚሊዮን 200 ሺህ የቤት እንስሳት ሞተዋል
- ከ604 ሺህ በላይ ሰዎች በመንግሥት እርዳታ እየተደረገላቸው ይገኛል

ዳግማዊት አበበ

አዲስ አበባ፡- በኦሮሚያ ክልል ቦረና ዞን በተከሰተው ድርቅ 807 ሺህ ሰዎች እርዳታ እንደሚያስፈልጋቸው የዞኑ አስተዳደር ገለጸ። በድርቁ ከሁለት ሚሊዮን በላይ እንስሳት መሞታቸው የተገለጸ ሲሆን ከ600 ሺህ በላይ ሰዎች በመንግስት ድጋፍ እየተደረገላቸው እንደሆነም ተጠቁሟል።

በኦሮሚያ ክልል የቦረና ዞን ዋና አስተዳዳሪ አቶ ጃርሶ ቦሩ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በዞኑ በተከሰተው ድርቅ 807 ሺህ ሰዎች እርዳታ ይፈልጋሉ። ከነዚህም ውስጥ 167 ሺህ የሚሆኑ ሰዎች አስቸኳይና ተከታታይ ድጋፍ የሚፈልጉ ሲሆን ሁለት ሚሊዮን 200 ሺህ ከብቶች ሞተዋል።

መንግሥት 604 ሺህ ለሚሆኑ ሰዎች እርዳታ እያደረገ እንደሚገኝ የገለጹት አቶ ጃርሶ፤ በዞኑ ለተከታታይ ሦስት ዓመታት በደረሰው ድርቅ ህብረተሰቡ አስከፊ ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ ተናግረዋል።

በድርቁ ከተጎዱት ከ800 ሺህ ሰዎች በላይ ውስጥ


በቦረና ዞን ... ወደ ገጽ 11 ዞሯል












ዶክተር ኤባ ሚጀና

## ዝቅተኛ ውጤት ላመጡ የ12ኛ ክፍል ተፈታኞች የአቅም ማሻሻያ ትምህርት ሊሰጥ ነው

ማህሌት ብዙነህ

አዲስ አበባ፡- በ2014 ዓ.ም የ12ኛ ክፍል ሀገር አቀፍ ፈተና ወስደው ከ50 በመቶ በታች ውጤት ላመጡ ከ106 ሺህ


ዝቅተኛ ውጤት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


# ባለሀብቶች በአነስተኛ ኤርፖርቶችና ሄሊፖርት ግንባታ ዘርፍ እንዲሳተፉ ጥሪ ቀረበ

ሞገስ ተስፋ

አዲስ አበባ፡- ባለሀብቶች በአነስተኛ የኤርፖርቶችና ሄሊፖርት ግንባታና አስተዳደር ዘርፍ እንዲሳተፉ የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለስልጣን ጥሪ አቀረበ:: በአቪየሽን ዘርፍ የተሰማሩ ባለሀብቶችን ለማበረታታት እየተሰራ እንደሚገኝም አመልክቷል::

የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለስልጣን ዋና ዳሬክተር አቶ ጌታቸው መንግስቴ ትናንት በሰጡት መግለጫ፤በኢትዮጵያ በኤርፖርቶችና ሄሊፖርት ግንባታና አስተዳደር ሥራ ላይ የባለሀብቶች ተሳትፎ ከሌሎች አገሮች ጋር ሲነጻጸር ዝቅተኛ ነው:: ከዚህ አኳያም ባለስልጣኑ ባለሀብቶች በአነስተኛ የኤርፖርቶችና ሔሊፖርት ግንባታና አስተዳደር ስራ ላይ እንዲሳተፉ ጥሪ


ባለሀብቶች በአነስተኛ ... ወደ ገጽ 11 ዞሯል




ፎቶ፡ ሃዲስ አብርሃ






## "የትግራይ ሕዝብ ዘላቂ ሰላም እንዲያገኝ ግልጽነት ያለው የሽግግር መንግስት ሊመሰረት ይገባል"

- አቶ ተሻለ ንጉስ

የትዴፓ የፖለቲካ ዘርፍ ኃላፊ




ገጽ 4



# የታሪካዊው ብስክሌተኛ ገረመው ደንቦባ ስርዓተ ቀብር ዛሬ ይፈፀማል

**ቦጋለ አበበ**

የታሪካዊው ብስክሌተኛ ገረመው ደንቦባ ስርአተ ቀብር ዛሬ በብርሃናተ ዓለም ጴጥሮስ ወጳውሎስ ቤተ-ክርስቲያን ከቀኑ 8 ሰአት ላይ ይፈጸማል። በኢትዮጵያ የብስክሌት ስፖርት እንዲሁም የኦሊምፒክ ተሳትፎ ታሪክ ደማቅ አሻራቸውን ካሳረፉ ድንቅና ግንባር ቀደም ስፖርተኞች አንዱ የሆኑት ብስክሌተኛ ገረመው ደንቦባ በሕክምና ሲረዱ ቆይተው ከትናንት በስቲያ በ90 ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት መለየታቸው ታውቋል፡፡

ታህሳስ 7 ቀን 1925 ዓ.ም በአዲስ አበባ የተወለዱት ብስክሌተኛ ገረመው፣ ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ በተሳተፈችበት እኤአ 1956 የሜልቦርን ኦሊምፒክ በብስክሌት ስፖርት ኢትዮጵያን ወክለው በመሳተፍ እና ሰንደቅአላማዋን በመያዝ ቀዳሚው አትሌት መሆናቸው ይታወቃል።

አንጋፋው ብስክሌተኛ ገረመው በሜልቦርን ኦሊምፒክ ተሳትፏቸው ኢትዮጵያ ከዓለም ዘጠነኛ ደረጃን ይዛ እንድታጠናቅቅ ያስቻሉበት ታሪክ በስፖርቱ ትልቅ ውጤት ሆኖ ይጠቀሳል።

እኤአ በ1960 የሮም ኦሊምፒክም እኚህ ታሪካዊ ብስክሌተኛ ተሳትፈው ከ11 ዙር ውስጥ 9ኙን በአንደኝነት እየመሩ ያሸንፋሉ ተብሎ ሲጠበቅ በድንገት ከኋላ ተገጭተው በመውደቃቸው አቋርጠው ለመውጣት ተገደው ነበር። ይህም በወቅቱ አንጋፋው ብስክሌተኛ ገረመው ተገቢ ያልሆነ ግጭት ባያስተናግዱ ማሸነፍ ይችሉ እንደነበር በዓለም ጋዜጦች ተዘግቦላቸዋል።

ገረመው ደንቦባ በቀጣዩ 1964 የቶኪዮ ኦሊምፒክም በዋና አሰልጣኝነት የኢትዮጵያን የብስክሌት ቡድን መምራት የቻሉ ሲሆን፤ በተወዳዳሪነት ዘመናቸው በተለያዩ አለም አቀፍ መድረኮች ከ 30 በላይ ዋንጫ እና 32 የወርቅ ሜዳሊያዎች ማስመዝገብ እንደቻሉ ከህይወት ታሪካቸው መረዳት ተችሏል።

ገረመው ደንቦባ በኢትዮጵያ ብስክሌት ስፖርት ታሪክ ውስጥ ትልቅ አሻራን ከማሳረፋቸው ባሻገር አቅማቸው ደክሞ እቤት መዋል እስከጀመሩበት ቅርብ ጊዜ ድረስ በተለያዩ መድረኮች እየተገኙ ልምዳቸውን በማካፈል ይታወቃሉ። ከእሳቸው በኋላ በኢትዮጵያ ብስክሌት ስፖርት ታሪክ ጎልተው መውጣት ለቻሉት እንደ ተሰማ አሞሳ፣ አድማሱ መርጋ፣ አላዛር ክፍሎም፣ጆቫኒ ማሶላ፣ጀማል ሮጎራና ጽጋቡ ገብረማርያም ለመሳሰሉ ብስክሌተኞች አርአያ መሆን ችለዋል።

# የገበያ ስርዓቱን ለማዘመን ከባንኮች ጋር መስራቱን እንደሚቀጥል የኢትዮጵያ ምርት ገበያ አስታወቀ

**ሄርሞን ፍቃዱ**




አዲስ አበባ፡- የገበያ ስርዓቱን ማዘመን ከአዳዲስ ባንኮች ጋር አብሮ መስራቱን እንደሚቀጥል የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ገለጸ።

የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ምክትል ስራ አስፈፃሚ አቶ መርጊያ ባይሳ የኢትዮጵያ ምርት ገበያ እና ሂጅራ ባንክ በትናንትናው ዕለት የክፍያ አጋርነት ስምምነት ሲፈራረሙ እንደገለጹት፤የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ከባንኮች ጋር በአጋርነት መስራቱ በተለይ አምራቹን ማህበረሰብ ተጠቃሚ በማድረግ የላቡን ዋጋ በወቅቱ እንዲያገኝና በግብይት ወቅት ሀገር ውስጥ የሚደረገው የገንዘብ እንቅስቃሴ ግልፅና ተጠያቂነት የተሞላበት እንዲሆን አስተዋፅኦ አድርጓል።

ባለፉት 15 ዓመታት ወደ ምርት ገበያው የመግዣ አካውንቶች ከገዢዎች ለግብይት የገባውና ለሻጮችም በምርት ገበያው አማካይ የተከፈለው የገንዘብ መጠን ከ350 ቢሊዮን ብር በላይ እንደሆነና፤ ለዚህም በ19 ባንኮች ውስጥ በአቅራቢዎችና በገዢዎች በተከፈቱት ከ11 ሺህ በላይ የባንክ አካውንቶች ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት እየተሰጠ ነው ብለዋል።

እስከ አሁን ከተቋሙ ጋር ሲሰሩ የቆዩ ባንኮች 19 የነበሩ ሲሆን፤ ሂጅራ ባንክ 20ኛው ባንክ አጋራችን መሆኑን ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ምርት ገበያ የኦንላይን ግብይት ለማሳደግ ከኢትዮጵያ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ጋር በቅርቡ የውል ስምምነት የፈረመ ሲሆን፤ ወደ ተግባር ሲገባ ባንኮች የአገልግሎት ጥራታቸው እንዲጨምርና የተገልጋይ ቁጥር ለማሳደግ አስተዋፅኦ እንደሚያደርግ ነው የተናገሩት አቶ መርጊያ።

የሂጅራ ባንክ ፕሬዚዳንት አቶ ዳዊት ቀኖ እንደተናገሩት፤ ሂጅራ ባንክ ከተቋቋመ አንድ ዓመት ተኩል ቢሆነውም አዲስ አበባን ጨምሮ 60 ቅርንጫፎች አሉት።ባንኩ ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ ጋር ያደረገው ስምምነት የክፍያ ስርዓቱ ይበልጥ ለማቀላጠፍና ለማዘመን የሚያደረገውን ጥረት ለማሳካት ትልቅ አስተዋፅኦ ከማድረጉም በላይ ተገበያዮች ግብይቱን በፈፀሙ ማግስት ገንዘባቸው በቀጥታ ከገዢው የባንክ ሂሳባቸው በማዞር ይረዳል።

ምርት ገበያው 20ኛው የክፍያ አጋር ከሆነው ሂጅራ ባንክ ጋር ስምምነት ሲፈራረም፤ ከአምራች አርሶ አደር እስከ አቅራቢው ድረስ ሁሉም የገበያው ተዋንያን ዘመናዊ የግብይት ስርዓት እኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ፤ የግብርና ምርቶች ግብይት ስርዓትን በማዘመን፤ ግልፀኝነትና መተማመንን በመፍጠር በሀገራችን የኢኮኖሚ ስርዓት ውስጥ ጉልህ ሚና ይኖረዋል ተብሏል።



# በስደት አስከፊነት ላይ ባተኮረው ሀገር አቀፍ የፊልም ውድድር አሸናፊዎች ተሸለሙ

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- በስደት አስከፊነት ላይ ባተኮረው የሀገር አቀፍ የፊልም ውድድር አሸናፊዎች በአውሮፓ ህብረት ሽልማት ተበረከተላቸው።

በስደት ላይ የሚያጋጥሙ እንግልቶችን በማስተማሪያነት ለማቅረብ ታስቦ በአውሮፓ ህብረት የተዘጋጀው አጭር የፊልም ውድድር የአሸናፊዎች ሽልማት ስነስርዓት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴያትር ትናንትና ተካሂዷል።

በሽልማት ስነ-ስርዓቱ ላይ ንግግር ያደረጉት በኢትዮጵያ የአውሮፓ ህብረት ልዑክ ቡድን መሪ አምባሳደር ሮላንድ ኮብያ፤ ውድድሩ የስደት እድሎችና ተግዳሮቶቹን አጉልቶ ከማሳየት ጎን ለጎን የኢትዮጵያን ወጣቶች የፈጠራ ክህሎት ለማሳደግና የስራ እድል ለማመቻቸት ያግዛል ብለዋል።

በውድድሩ ስድስት የአንድ ደቂቃ አስተማሪ ፊልሞች የተመረጡ ሲሆን፤ ከአንድ እስከ ስድስት የወጡ ተወዳዳሪዎች ሽልማት እንደተበረከተላቸው ገልጸዋል።

የውድድሩ አላማ ስለስደት አስከፊነት ወጣቱ እንዲገነዘብና ስለጉዳዩ በነጻነት እንዲወያይ ለማበረታታት ነው ያሉት አምባሳደሩ፤ የአውሮፓ ህብረት በኢትዮጵያና በአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ያለውን ህገወጥ የስደት እንቅስቃሴ ለመቀነስ ከአካባቢው ሀገራት ጋር በትብብር ይሰራል ብለዋል።

አምባሳደሩ አክለውም፤ በህገወጥ የስደት አስከፊነት ላይ አስተማሪ መልዕክት ለማስተላለፍ ታስቦ የተዘጋጀው ውድድር ወጣት ኢትዮጵያውያን በአንድ ጠቃሚ ርዕስ ላይ ሃሳባቸውን እንዲገልጹ እድል ፈጥሯል ሲሉ ተናግረዋል።

እንደ አምባሳደሩ ገለጻ፤ የአውሮፓ ህብረት ከ2015 እ.ኤ.አ ጀምሮ ከስደት ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ ለኢትዮጵያ የሚሰጠው ድጋፍ በአውሮፓ ህብረት የአደጋ ጊዜ ትረስት ፈንድ (EUTF) በኩል ተፈጻሚ ሲያደርግ ቆይቷል።

ህብረቱ ለዜጎች መፈናቀልና እና ለስደት መንስኤዎች የሆኑ ጉዳዮችን ለመፍታት እንዲሁም የተሻለ የፍልሰት አስተዳደር እንዲፈጠር በሚያግዙ ስራዎች ላይ የበኩሉን አስተዋጽኦ እያበረከተ ይገኛል ብለዋል፡፡

ስደት መቀነስ ቢቻል እንጂ ሙሉ በሙሉ ማስቀረት አይቻልም ያሉት አምባሳደሩ፤ ችግሮች እንዳይባባሱና ሰብዓዊ አገልግሎቶች እንዲስፋፉ የአውሮፓ ህብረት ቀድሞ ከሚያደርገው ድጋፍ በበለጠ ትኩረት ሰጥቶ እንደሚሰራ አስታውቀዋል።

የአውሮፓ ህብረት የኢትዮጵያ ልዑክ ቡድን ከታህሳስ ወር 2022 እ.ኤ.አ ጀምሮ ዓለም አቀፍ የስደተኞች ቀንን በማስመልከት ‹‹የስደት እድሎች እና ተግዳሮቶች›› በሚል መሪ ሀሳብ አጭር የፊልም ውድድር በኢትዮጵያ ሲያካሂድ እንደነበር የሚታወስ ነው።

በውድድሩ እድሜያቸው ከ15 እስከ 35 የሆኑ ኢትዮጵያውያን መሳተፋቸው ታውቋል። የአውሮፓ ህብረት ልዑክ ቡድን መሪ አምባሳደር ሮላንድ ኮብያ፣ የፋሽን ባለሙያና ስራ ፈጣሪ ማህሌት አፈወርቅና አርቲስት ካስማሰ የውድድሩ አሸናፊዎችን ምርጫ አካሂደዋል።

ወድድሩን ካሸነፉት ስድስት ተወዳዳሪዎች መካከል ተስፋማርያም ዳርጌ አንደኛ ደረጃን የያዘ ሲሆን፤ በሀገራችን በተገኘው ሰላም አማካኝነት ቤተሰቦቹ ከመቀሌ መጥተው የደስታዬ ተካፋይ በመሆናቸው ድርብ ደስታ ፈጥሮልኛል ብሏል።

ዜና

# በስልጤ ዞን ከ17 ሺህ ሄክታር መሬት በላይ የተፋሰስ ልማት ስራ ተከናውኗል

## - በ35 ቀናት ከ38ሺህ በላይ ሄክታር መሬት ለማልማት ታቅዷል

ዳግማዊት ግርማ



ሁልባረግ (ስልጤ)፡- በስልጤ ዞን ኅብረተሰቡን በማሳተፍ በ15 ቀናት ብቻ 17ሺህ ሄክታር መሬት የተፋሰስ ልማት ስራ መከናወኑን የዞኑ ግብርና መምሪያ ገለፀ። በስልጤ ዞን ሁልባረግ ወረዳም ህብረተሰብ አቀፍ የተፋሰስ ልማት ንቅናቄ ተካሂዷል።

በቢሮው የተፈጥሮ ዘርፍ ኃላፊ አቶ ሀያቱ ሙከታር በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በዞኑ በተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃ ላይ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ ይገኛል፡፡ በዚህም ህብረተሰቡን በማሳተፍ በ15 ቀናት ብቻ ከ17 ሺህ ሄክታር በላይ መሬት የተፋሰስ ልማት ስራ ማከናወን ተችሏል።

ለመጪው ክረምት የሚተከሉ ችግኞችን የማዘጋጀት ስራ፣ የአፈርና ውሃ ዕቀባ እና የተተከሉ ችግኞችን መንከባከብ በተፋሰስ ልማት ስራ የሚከናወኑ ተግባራት መሆናቸውን ጠቅሰዋል።

እንደ ኃላፊው ገለጻ፤ በህብረተሰብ አቀፍ የተፋሰስ ልማት በ35 ቀናት 38 ሺህ በላይ ሄክታር መሬት የአፈርና የውሃ ልማትና ጥበቃ ለማካሄድ ታቅዶ ለህዝቡ በይፋ ከተበሰረበት ጥር 27 ቀን 2015 ጀምሮ ባሉት 15 ቀናት ውስጥ ብቻ 17 ሺህ 339 ሄክታር መሬት መሸፈን ተችሏል።

በውስን ቀናት 344 ሺህ ዜጎችን ባሳተፈ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃ እንቅስቃሴም የእቅዱን 44 ነጥብ 8 በመቶ ማሳካት መቻሉንም ኃላፊው ጨምረው ገልጸዋል።

83 ሚሊዮን የዘርፈ-ብዙ ጠቀሜታ ያላቸውን የጥምር ደን፣ የፍራፍሬ ፣ የቡና፣ የመኖና የቀርከሃ የችግኝ ብዜት ለማካሄድ ታቅዶ እስከ የካቲት 12 ቀን 2015 ድረስ 37 ነጥብ 6 ሚሊዮን ችግኝ ማፍላት መቻሉን አቶ ሀያቱ ተናግረዋል፡፡

ከዕቅዱ ቀሪው የችግኝ ብዜት ስራ በቀሪ ቀናት ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል ያሉት አቶ ሀያቱ፤ በተለይም የእንስሳት መኖ ለማባዛት የታቀደውን እና በአጭር ጊዜ የሚደርሱ የዛፍ ዝርያዎች ላይ ትኩረት በመስጠት በቀጣዮቹ ሳምንታት የሚከናወን ይሆናል ብለዋል።

በያዝነው የየካቲት ወር 2015ዓ.ም የተጀመረው የተፋሰስ ልማት "የተቀናጀ የተፋሰስ ልማት ለብልጽግናችን" በሚል መሆኑን ገልጸው፤ ይህን ህዝባዊ ንቅናቄ የሠላሳ አምስት ቀናት ቆይታ እንደሚኖረውም አቶ ሀያቱ አመልክተዋል።

የሁልባረግ ወረዳ ምክትል አስተዳዳሪና በወረዳው የግብርና ፅህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ሙባረክ ኑርከባ በበኩላቸው፤ ወረዳቸው በተፋሰስ ልማት በትኩረት እየተሰራ መሆኑን አመልክተው፤ በወረዳው በሚገኙ 10 ቀበሌዎች ተግባራዊ እየተደረገ ያለው ኅብረተሰብ አቀፍ ተፋሰስ ልማት አንድ ሺህ 400 ሄክታር መሬት ለማልማት ታቅዶ በ15 ቀናት ውስጥም 525 ሄክታር መሬት መልማቱን ተናግረዋል።

ኅብረተሰብ አቀፉ የተፋሰስ ልማት በአካባቢ ጥበቃና በአፈር ለምነትና በውሃ መጠን ላይ ከፍተኛ የሆነ አዎንታዊ አስተዋፅኦ እንደሚኖረውም አቶ ሙባረክ ተናግረዋል።



# ዓለም አቀፍ አውደ ርዕዩ

## የአገር ውስጥ አምራቾችን ከውጭ ገበያ ጋር ለማስተሳሰር ይረዳል

ማርቆስ በላይ

አዲስ አበባ፡- 25ኛው አዲስ ቻምበር ዓለም አቀፍ አውደ ርእይ የአገር ውስጥ አምራቾችን ከውጭ ገበያ ጋር ለማስተሳሰር እንደሚረዳ ተገለጸ።

የአዲስ አበባ ንግድ ምክር ቤት ያዘጋጀው ዓለም አቀፍ የንግድ አውደ ርእዩ በኢግዚቢሽን ማዕከል ትናንት ተከፍቷል።

የንግድ እና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ዴኤታ አቶ እንዳለ መኮንን በወቅቱ እንደገለጹት፤ በአዲስ ቻምበር አዘጋጅነት የተሰናዳው አውደ ርእይ የአገር ውስጥ የንግድ እንቅስቃሴዎችን ለማሳደግ ወሳኝነቱ የጎላ ነው።

በአውደ ርእዩ የተለያዩ የሀገር ውስጥ ምርቶችን ለማገበያየትና የንግድ ሃሳብ ልውውጥ ለማካሄድ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል። የአገር ውስጥ አምራቾች ከሌሎች መሰል አምራቾችና አስመጪዎች ጋር በቀጥታ የሚገናኙበት መድረክ በመሆኑ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ አለው ብለዋል።

አቶ እንዳለ እንደገለጹት፤ዓለም አቀፉ የአዲስ ቻምበር የንግድ አውደ ርእዩ ከየካቲት 16 እስከ 20 ይካሄዳል። በመድረኩ ምርትና አገልግሎቱን ማቅረብ የሚፈልግ ተቋምና ግለሰብ የንግዱ እንቅስቃሴውን ለማሳደግ የሚረዳ ግብዓት ይገኝበታል ተብሎ ይታመናል።

ዓለም አቀፍ አውደ ርእይ በመዲናዋ መካሄዱ የአገር ውስጥ አምራቾች ከውጪ አምራቾች ጋር እንዲገናኙና የልምድ ልውውጥ እንዲያካሂዱ ዕድል ይፈጥራል። መንግስት ተመሳሳይ መድረኮች በቀጣይ ተጠናክረው እንዲቀጥሉ አስፈላጊውን ድግፍ ያደርጋል ሲሉ አስታውቀዋል።

የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ወይዘሮ መሰንበት ሸንቁጤ በበኩላቸው እንደገለጹት፤የዓለም አቀፍ አውደ ርእዩ አላማ የኢትዮጵያን አምራቾች ከውጪ አምራቾች ጋር ተባብረው ምርቶችን ወደ ውጪ በመላክ ተቀባይ እንዲያገኙ የሚያስችል ግንኙነት ለመፍጠር ነው።

በአገሪቱ በተለያዩ ዘርፎች የተሰማሩ በርካታ አምራቾች መኖራቸውን የገለጹት ወይዘሮ መሰንበት፤ ከውጪ አገር ገበያው ጋር አገናኝ ባለመኖሩ ምክንያት በገበያ እጦት ሲቸገሩ እንደሚስተዋል ጠቁመዋል።

የገበያ እጦትና የልምድ ልውውጥ እጥረቶችን ለመቅረፍ ዓለም አቀፍ አውደ ርእዮች አስፈላጊ ናቸው። በአዲስ አበባ በተዘጋጀው የንግድ አውደ ርእይ ላይ ድርጅቶች ከገበያ ትስስር ባለፈ የቴክኖሎጂውን ሽግግር ለማግኘት እድል ተፈጥሮላቸዋል ብለዋል።

በ25ኛው አዲስ ቻምበር ዓለም አቀፍ የንግድ ትርኢት ላይ 53 የውጭ አገር አምራቾች እና 23 የአገር ውስጥ አምራቾች እየተሳተፉ መሆኑን በመግለጽ፤ በመድረኩ መሳተፍ ያልቻሉ የአገር ውስጥ አምራቾች በኤግዚቢሽን ማዕከል በመገኘት የንግድ ግንኙነታቸውን ማስፋት እንደሚችሉ አስታውቀዋል።

የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት (አዲስ ቻምበር) ከኢትዮ አሜሪካ ቻምበር ኦፍ ኮሜርስ ጋር በጋራ ለመስራት የሚያስችላቸውን የመግባቢያ ስምምነት መፈራረሙ የሚታወስ ነው።

# በ23 ከተሞች ንፁህ የመጠጥ ውሃን ለማዳረስ የሚረዱ ፕሮጀክቶች እየተከናወኑ ነው

ቃልኪዳን አሳዬ

አዲስ አበባ፡- በ23 ከተሞች የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦትን በተሻለ መንገድ ለማዳረስ የሚረዱ ፕሮጀክቶች እየተከናወኑ መሆኑን የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር አስታወቀ።

የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሪ ስራ አስፈጻሚ አቶ ታምሩ ገደፋ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ ከአዲስ አበባና ድሬዳዋ በተጨማሪ በክልል ዋና ዋና ከተሞች የንጹህ መጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች እየተተገበሩ ነው።

በጎንደር፣ ጅማ፣ አዳማ፣ ሐዋሳ፣ ባህር ዳር፣ ጅግጅጋ፣ ሰመራ፣ ጋምቤላ፣ አሶሳና በተለያዩ ከተሞች ላይ የውሃ ፕሮጀክቶቹ እየተከናወኑ ይገኛል። የየፕሮጀክቶቹ አፈጻጸም ደረጃ የተለያየ ቢሆንም በዘንድሮው ዓመትና በቀጣይ ዓመት የሚጠናቀቁ አሉ። ሁሉንም ፕሮጀክቶች ለማጠናቀቅ ደግሞ አራት ዓመታት ያስፈልጋሉ ብለዋል።

በከተሞች አካባቢ ለሚከናወኑት የውሃ ፕሮጀክቶች 70 ሚሊዮን ዶላር በጀት ተመድቦ ጥቅም ላይ እየዋለ ይገኛል ሲሉም ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ ካላት የውሃ ሀብት አንፃር የንጹህ መጠጥ ውሃ አቅርቦቱ አነስተኛ በመሆኑ አቅርቦቱን በከተማም ሆነ በገጠር የማሳደግ ክንውን ያስፈልጋል ሲሉ አስረድተዋል።

በሚያጋጥመው የንጹህ መጠጥ ውሃ እጥረት የተነሳ በተወሰኑ ከተሞች ላይ የውሃ አቅርቦቱ በፈረቃ የሚዳረስበት አጋጣሚ ሰፊ ነው ብለዋል።

ችግሩም የፍላጎትና አቅርቦት አለመመጣጠንን ያሳያል። የከርሰምድርና ገፀ ምድር የውሃ ሃብቶችን በመጠቀም አቅርቦትን ለማሳደግ የሚረዱ የውሃ መሰረተ ልማት ግንባታዎች በተለያዩ ከተሞች ላይ እየተከናወነ መሆኑን ገልጸዋል።



አቶ ታምሩ ገደፋ

አቶ ታምሩ እንዳስታወቁት፤ በቀጣይ የአስር ዓመት እቅድ መሰረት ሁሉም ዜጋ በአቅራቢያው የንጹህ መጠጥ ውሃ ተጠቃሚ እንደሚሆን ይጠበቃል።

የህብረተሰቡ ቁጥር ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ ስለሚሄድ ከፍላጎቱ ጋር የሚመጣጠን የውሀ ፕሮጀክት ግንባታና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት የማሳደግ ስራ ያስፈልጋል። ለዚህም መንግስት ከአጋር ተቋማት ጋር በመተባበር የውሃ አቅርቦትን የሚያሳድጉ ስራዎችን በየጊዜው እያከናወኑ ይገኛል ብለዋል።

አቶ ታምሩ እንደገለጹት፤ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የውሃ ስርጭቱን አንድ ቦታ ሆኖ ለመቆጣጠር የሚረዳ ፕሮጀክት ዕውን ለማድረግ እንቅስቃሴ ጀምሯል። ይህን በከተማና በገጠር ያለውን የውሃ ሃብት በቅንጅት በመምራት የንጹህ መጠጥ ውሃ ተደራሽነትን ለማሳደግ ይረዳል።

በከተማ የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶቹ ንፁህ ውሃን ከማዳረስ ባለፈ በዋናነት የውሃ ብክነትን ለመቀነስ የሚረዱ የተለያዩ ስራዎች ለህብረተሰቡ በመከናወን ላይ እንደሚገኙ ጠቁመዋል።

በሁለተኛው የከተሞች የውሃና ንጽህና አቅርቦት ፕሮጀክት አማካኝነት የውሃ ብክነትን የሚከላከል ስራ እየተከናወነ ይገኛል። የውሃ አቅርቦቱ በዘመናዊ የቴክኖሎጂ ስርዓት እንዲመራ የሚያስችል ፕሮጀክት እየተሰራበት ነው ብለዋል።

በከተሞች አካባቢ የሚባክነውን የንፁህ መጠጥ ውሃ ከብክነት ከመከላከል ባለፈ የታዳሽ ሃይል አጠቃቀምን የማሳደግ ስራም እየተከናወነ መሆኑን ጠቁመዋል።

በገጠራማ ቦታዎች ላይ ውሃን ከረጅም ርቀት ለመሳብ የሚያስፈልገውን የነዳጅ ሃይል ወደ ጸሐይ ሃይል በመቀየር ወጪን መቀነስ የሚያስችል ስራ መከናወኑንና ትግበራው በከተሞች አካባቢም ውጤት ማምጣቱን አስታውቀዋል።

ለህብረተሰቡ በቂ የንፁህ መጠጥ ውሃ ተደራሽ ለማድረግ በሚከናወኑ ስራዎች ላይ የበጀት እጥረት፣ በዘርፉ ያሉ ኮንትራክተሮች አቅም ውስንነት፣ የግብዓት እጥረትና የፀጥታ ችግር ፈተና መሆናቸውን ጠቁመዋል።

ችግሮቹን ለመፍታት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በተለያዩ ጊዜያት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመነጋገር እየሰራ ነው ያሉት አቶ ታምሩ፤ በሌላ በኩል በጀትን ለማሳደግ የሚረዱ በጎ እንቅስቃሴዎች ከውጭ አገር ተቋማት ጋር እየተከናወኑ መሆኑን ተናግረዋል።

ዜና

# “የትግራይ ሕዝብ ዘላቂ ሰላም እንዲያገኝ ግልጽነት ያለው የሽግግር መንግስት ሊመሰረት ይገባል”

**- አቶ ተሻለ ንጉስ**
**የትዴፓ የፖለቲካ ዘርፍ ኃላፊ**

**ሄርሞን ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- በትግራይ ክልል ዘላቂ ሰላም እንዲመጣ ግልፅነት ያለው አካሄድን የተከተለ የሽግግር መንግስት ሊመሰረት ይገባል ሲሉ የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ትዴፓ) የፖለቲካ ዘርፍ ኃላፊ አቶ ተሻለ ንጉስ ገለፁ፡፡

አቶ ተሻለ ንጉስ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ለትግራይ ህዝብ የተሟላ እና ዘላቂ ሰላም እንዲረጋገጥ በፕሪቶሪያው ስምምነት መሰረት የሽግግር መንግስት ማቋቋም ወሳኝ ነው፡፡ ለዚህም ግልጽነት ያለው አካሄድ የተከተለ የሽግግር መንግስት ሊመሰረት ይገባል፡፡

የሽግግር መንግስት ምስረታው በአፋጣኝ እንዲፈፀም በስምምነቱ ላይ የነበሩ አካላት፣ የትግራይ ህዝብ ፣ ፖለቲከኞች እና ዲያስፖራው የድርሻቸውን መወጣት አለባቸው፡፡

የሽግግር መንግስቱ በጊዜው ስላልተተገበረና በዚህ ምክንያት በጀት ባለመለቀቁ ሕዝብ በከፍተኛ ችግር ውስጥ ይገኛል ያሉት አቶ ተሻለ፤ ሕዝቡ ተስፋ የጣለበት ሰላም እንዳይቀለበስ በትግራይ ክልል የሽግግር መንግስቱን የመመስረት ጉዳይ ሳይዘገይ ግልጽና አሳታፊ በሆነ መንገድ ሊተገበር ይገባል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

የትግራይ ሕዝብ የተሟላ እና ዘላቂ ሰላም ሊያገኝ የሚችለው፤ዲሞክራሲያዊና አሳታፊ በሆነ መንገድ የሽግግር መንግስት ሲመሰረት ነው ብለዋል፡፡

የሽግግር መንግስት ምስረታው ለሕዝብ ያለው ጠቀሜታ ከፍተኛ በመሆኑ፤ ሕዝቡ ከመንግስት ጎን በመሆን ዲሞክራሲያዊ መብቱን ለማረጋገጥ በንቃት ሊሳተፍ ይገባል፤ ሕዝቡ የሚፈልገውን ዘላቂ ሰላም ሊያገኝ የሚችለው በስምምነቱ ላይ የተካተቱ ነጥቦች በትክክል ሲተገበሩ እንደሆነም ገልፀዋል፡፡

የሚመሰረተው ሽግግር መንግስት ብዝሃ ሃሳብን የሚያስተናግድ እና በሕዝቡ ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረው የገለልተኛ አካላት ፣የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ምሁራን፣ ዲያስፖራው እንዲሁም ሲቪክ ማህበራት ተሳትፎ ወሳኝ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ከዚህ በፊት የተለያየ የፖለቲካ እሳቤን የሚያስተናግድ አደረጃጀት አልነበረም። በዚህ ምክንያትም የትግራይ ሕዝብ አማራጭ ሳያገኝ ለ30 ዓመታት ቆይቷል። ይህ እንዳይደገም ምሁራኑ ከፍተኛ ኃላፊነት ስላለባቸው ግዴታቸውን ሊወጡ ይገባል ነው ያሉት አቶ ተሻለ፡፡

የትግራይ ሕዝብም እስከ መጨረሻ ድረስ ድጋፉን ሊያጠናክር ይገባል ያሉት አቶ ተሻለ፤ የፌዴራል መንግስት የትግራይ ሕዝብ የተሟላ ሰላም እንዲያገኝ የተቻለውን እያደረገ ቢሆንም፤ ሁሉም ችግሮች በመንግስት ብቻ ስለማይቀረፉ ሕዝብ ከመንግስት ጎን መቆም አለበት ሲሉ ተናግረዋል፡፡

አሁን ድረስ የሽግግር መንግስት በወቅቱ ባለመመስረቱ የመንግስት ስራ አልተጀመረም፤ ስለሆነም ሕዝቡ፣ የትግራይ ዲያስፖራና የፖለቲካ ፓርቲዎች አፋጣኝና ግልጽ በሆነ መንገድ የሽግግር መንግስት ምስረታው እንዲካሄድ ድጋፍ ማድረግ እንዳለባቸው አሳስበዋል፡፡

# ዝቅተኛ ውጤት ሳመጡ የ12ኛ ክፍል ተፈታኞች...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

በላይ ተፈታኞች ለመጀመሪያ ጊዜ የሚሰጠው የአቅም ማሻሻያ (ሪሚዲያል) ትምህርት ፕሮግራም ለአራት ወራት ያህል በሀገሪቱ በሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች እንደሚሰጥ የትምህርት ሚኒስቴር ገለጸ፡፡

በትምህርት ሚኒስቴር የአካዳሚክ ጉዳዮች መሪ ስራ አስፈጻሚ ዶክተር ኤባ ሚጀና ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በ2014 የትምህርት ዘመን የ12ኛ ክፍል ማጠቃለያ አገር አቀፍ ፈተና ወስደው ከ50 በመቶ በታች ውጤት ያስመዘገቡ ተማሪዎች የአቅም ማሻሻያ (ሪሚዲያል) ፕሮግራም ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፣ከአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ እና አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ውጪ ባሉ ሁሉም የመንግስት እና የግል ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ ለአራት ወራት ይሰጣል፡፡

ዶክተር ኤባ ይህ መርሀ ግብር ከዩኒቨርሲቲዎች የተውጣጡ ባለሙያዎች እና ፕሮፌሰሮች ኮሚቴ በማዋቀር ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ያሉት የትምህርት አይነቶች ትኩረት በማድረግ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ማወቅ ያለባቸውን አስፈላጊ እና ጠቃሚ የሆኑ የትምህርት ይዘቶችን በመለየት ለተቋማት አድርሰናል ብለዋል፡፡

በዚህ አቅም ማሻሻያ (ሪሚዲያል) ፕሮግራም የተፈጥሮ ሳይንስ ተማሪዎች ፊዚክስ፣ ባዮሎጂ፣ ኬሚስትሪ፣ እንግሊዘኛ፣ የተፈጥሮ ሳይንስና የሂሳብ የትምህርት አይነቶችን የሚወስዱ ሲሆን፤ማህበራዊ ሳይንስ ተማሪዎች ታሪክ፣ጂኦግራፊ፣ እንግሊዘኛ ፣ማህበራዊ ሳይንስና ሂሳብ ትምህርቶችን ለአራት ወራት እንደሚወስዱ ዶክተር ኤባ ተናግረዋል፡፡

በእነዚህ የትምህርት ይዘቶች መሰረት በተቋማት የሚዘጋጅ ከ30 በመቶ እና በማእከል የሚዘጋጅ ከ70 በመቶ የሚያዝ ፈተና በመፈተን በድምሩ 50 በመቶ እና ከዛ በላይ የሚያገኙ ተማሪዎች በማሳለፍ የመደበኛ የዩኒቨርሲቲ ትምህርት ይቀጥላሉ፡፡ በተጨማሪም ከመንግስት ወደ ግል ዩኒቨርሲቲዎች በማዘዋወር ትምህርታቸውን መቀጠል ይችላሉ፡፡

የአቅም ማሻሻያ ፕሮግራም ትምህርቱ ያስፈለገው ፈተናው በዚህ አይነት አግባብ ለመጀመሪያ ጊዜ የተመራ በመሆኑ፣ ተማሪዎች ከቤተሰብ ርቀው ወደሌላ ተቋም ተጉዘው ስለነበር የስነልቦና ዝግጅት ላይ ክፍተት ሊኖር ስለሚችል እንዲሁም ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የመቀበል አቅም ግምገማ በማገናዘብ የተወሰነ ውሳኔ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

ዶክተር ኤባ እንደገለጹት፤ በዚህ መርሀ ግብር 106 ሺ ተማሪዎች ትምህርቱን እንደሚወስዱ አስታውሰው፤ ትምህርታቸውን በመንግስት በጀት በአግባቡ እና በተሻለ መልኩ በመከታተል ሰፊ የሆነ የማለፍ እድል እንዲኖር ከማድረግ በተጨማሪ ለትምህርት ጥራት አዎንታዊ ሚና አለው ብለዋል፡፡

ዘንድሮ የተገኘው ውጤት እጅግ በጣም ዝቅተኛ ከመሆኑ የተነሳ በየትምህርት ቤቱ ያለው የትምህርት ጥራት ምን እንደሚመስል ቁልጭ አድርጎ ያሳየ ነው ያሉት ዶክተሩ፤ ከክፍል ወደ ክፍል ተማሪዎች በሚያልፉበት ጊዜ ምን አይነት እውቀት ይዘው ሲያልፉ እንደነበር ፣ የፈተና ስርአቱ እንዴት ሲካሄድ እንደቆየ፣እያንዳንዱ ተቋም እንዴት እንደሚመራ እና የሀገሪቱ የትምርት ጥራት ምን ደረጃ ላይ እንዳለ ግልጽ አድርጎ ያስቀመጠ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

እንደ ዶክተር ኤባ ገለጻ፤ ለወደፊቱም በአጠቃላይ የሀገሪቱን የትምህርት ስርዓት በአግባቡ መፈተሽ አለብን የሚል አቅጣጫ ተቀምጧል፡፡ በዚህ መሰረትም በትምህርት ስርአት ውስጥ ያሉ ችግሮችን በመለየት እነሱን የማስተካከል ስራ እንዲሁም ተማሪዎች ከታች ጀምሮ በአግባቡ ተገቢ እውቀት አግኝተው እንዲያልፉ ለማድረግ ይሰራል፡፡

ዘንድሮ አጠቃላይ 136ሺ ተማሪዎች በየዩኒቨርሲቲዎች የሚመደቡ ሲሆን፤ ይህንን ድጋሚ የማይገኝ እድል ያገኙ ተማሪዎች በአግባቡ እንዲጠቀሙበት መልእክት አስተላልፈዋል፡፡



# ርዕሰ አንቀፅ

## ስነገ ሕልሞቻችን ስኬት የወጪ ንግድን ማሳደግና ማስፋፋት ወሳኝ ነው!

መንግስት ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ ሲንቀሳቀስባቸው ከነበሩ ትላልቅ ፕሮጀክቶች አንዱ ሀገራዊ የስንዴ ምርትን በመጠን እና በጥራት በማሳደግ፤ ሀገርና ሕዝብን በተሻለ ሁኔታ ተጠቃሚ ማድረግ ነው። በዚህም እስካሁን ባለው አፈጻጸም እየተመዘገበ ያለው ውጤት አበረታችና ዓለም አቀፍ እውቅና የተቸረው ነው።

መንግስት መላው ሕዝባችንን አስተባብሮ የጀመረውንን ይህን ፕሮጀክት በቁርጠኝነት ማስቀጠል ከቻለ ፤ ብዙ የትናንት የተመፅዋችነት ታሪኮቻችን እና እነዚሁ የፈጠሩት የልብ ስብራቶች የሚፈወሱበትና አዲስ የታሪክ ትርክት የሚጀመርበት ጊዜ ሩቅ እንደማይሆን ይታመናል።

ሀገራችን ለስንዴ ምርት ካላት ተስማሚ የአየር ንብረት እና በቂ የውሃ አቅርቦት አንጻር፤ እስካሁን የዚህ ተፈጥሮ ሀብት ተጠቃሚ አለመሆኗ በብዙ መልኩ የሚያስቆጭ ነው፤ ይህም ሆኖ ግን አሁንም ዓይናችንን ከፍተን ሀብቱን መጠቀም በሚያስችል ቁመና ላይ መገኘታችን የሚበረታታ ነው።

በተለይም በስንዴ ማምረት ላይ የተሰማራው አርሶ አደር ፕሮጀክቱ የእርሱን ሕይወት በመለወጥ፤ ሀገርን ወደ አዲስ የታሪክ ምእራፍ የማሻገር ራእይ ያነገበ መሆኑን ተገንዝቦ፤ ለልማቱ ልዩ ትኩረት በመስጠት እያደረገ ያለው ተሳትፎና እያስመዘገበ ያለው ውጤት ከፍ ያለ እውቅና የሚቸረው ነው።

ይህን ተሳትፎውን ምርቱ ለውጪ ገበያ ማቅረቡን ተከትሎ በተለያዩ መንገዶች እየተካሄዱ ካሉ የሴራ ፕሮፓጋንዳዎች እና ውዥንብሮች በመጠበቅ፤ መንግስት የጀመረውን ይህን ትውልድ ተሻጋሪ ፕሮጀክት በተሻለ መልኩ ውጤታማ እንዲሆን በትጋት መንቀሳቀስ ይጠበቅበታል።

ፕሮጀክቱ ከፍ ባለ የውጪ ምንዛሬ / የመንግስት የግብርና ኢንቨስትመንት /የሚካሄድ ነው፤ ፕሮጀክቱን ለማስቀጠል ሆነ አሁን ካለበት ከፍ ወዳለ ደረጃ ለማሸጋገር ተጨማሪ የውጪ ምንዛሬ ይጠይቃል፤ ይህን እውን ለማድረግ ደግሞ ቢያንስ ቢያንስ የተወሰነውን ምርት ወደውጭ በመላክ የውጪ ምንዛሬ አቅምን ማሳደግ የግድ ነው።

ይህን ማድረግ ካልተቻለ በቀጣይ የስንዴ ልማቱን በተጀመረበት ልክ ለማስቀጠል የሚያስችል አቅም ሊኖር አይችልም ፤ ይህ ደግሞ በተለይ ምርቱን በማምረት የተሻለ ተጠቃሚ ለሆነው፤ ነገ ላይም የላቀ ተጠቃሚነት ተስፋ ለሚያደርገው ገበሬ ታይቶ እንደሚጠፋ ብርሃን / ተስፋ/ ያህል ሆኖ ማለፉ የማይቀር ነው።

እንደ ሀገርም በብዙ ቁርጠኝነትና ከፍ ያለ ዋጋ "አይቻልምን ወደ ይቻላል" የለወጠውን ታሪካዊ ክስተት ሊያደበዝዝ የሚችል፤ መጪውም ትውልድ ነገዎቹን በተሻሉ ዛሬዎች ላይ እንዳያዋቅርና በተለመደውና በተመጣበት የአይቻልም መንገድ እንዲቀጥል የሚያስገድደው ይሆናል።

በርግጥ ላለፉት ግማሽ ምእተ አመታት በላይ የስንዴ ፖለቲካ ዓለምን ካስከፈለው ዋጋ አንጻር፤ ዛሬ በስንዴ ምርት ራሳችንን ችለን ምርቱን ለውጭ ገበያ ለማቅረብ እየሄድንበት ያለው መንገድ አልጋ በአልጋ ይሆናል ብሎ መገመት የዋህነት እንደሚሆን ይታመናል።

ከዚህ አንጻር ስንዴ ለውጭ ገበያ ማቅረባችንን ተከትሎም ሆነ ሀሳቡ ከተነሳ ጀምሮ እየተካሄደ ያለው የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ፤ በብዙ መልኩ ተጠባቂ ነው፤ ጉዳዩን የፖለቲካ አጀንዳ አድርጎ ለመውሰድ የሚደረገው ጥረት ግን ፈጽሞ ተቀባይነት የሌለውና፤ የሀገርንና የሕዝብን ጥቅም አሳልፎ እንደመስጠት የሚቆጠር ነው።

ሀገራት ሁሉ ምርቶቻችውን ለውጭ ገበያ የሚያቀርቡት፤ ምርቱ ተርፏቸው፤ ተትረፍርፏቸው ነው ተብሎ አይታመንም። በተለይም ራሳቸውን ለመለወጥ በብዙ መልኩ ደፋ ቀና የሚሉ ሀገራት ስለነገዎቻቸው አምጠው ያለሟቸውን ሕልሞች እውን ለማድረግ ከጉድለታቸውም ቢሆን ያላቸውን ይዘው የዓለም ገበያን መደባለቃቸው የተለመደ ነው። የኛም ቢሆን ከዚሁ እውነታ የተለየ አይደለም።

ለሀገር ጠቃሚው መንገድ ኢትዮጵያን የሚመጥን ታላቅ ራዕይ መሰነቅ፤ ለዚሁ ራዕይ መሳካት መተባበርና ፈተናዎችንና ተግዳሮቶችን በጥበብ እያለፉ መጓዝ ነው። ከዚህ አንጻር የስንዴ ልማቱም ሆነ የኤክስፖርት ጅማሬው ይበል የሚሰኝና ተጠናክሮና ይበልጥ ውጤታማ ሆኖ ሊቀጥል የሚገባው ነው!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

## የካቲት ወርና ጥቁር ሕዝቦችን ምን አገናኛቸው?

ስምስም መንግሥቱ

የ13 ወራት ፀጋ ባለቤት የሆነችው ኢትዮጵያ ወራቶቿም የሕዝብ ለሕዝብ ትስስር፣ የሀገር ፍቅር ስሜት በመፍጠር በባህል፣በእምነት፣ በታሪክ፣ የተከፋፈለ እሴት ያላቸውና የሚተነተኑ የሌላውንም ዓለም ቀልብ የሚስቡ ናቸው። በዚህ ረገድ በዋናነት ከሚጠቀሱት ወራቶች ያሳለፍነው ጥር እና የያዝነው የካቲት ወራቶች ይጠቀሳሉ።

በማይዳሰስ ቅርስ በተባበሩት መንግሥታት የሳይንስ፣ የትምህርትና የባህል ድርጅት (ዩኔስኮ) የተመዘገበው በኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች የተከበረው የጥምቀት በዓል ከአንዱ ነው፣ በዓሉ ያለው መንፈሳዊ፣ በማህበራዊ ፋይዳ ከመላው ዓለም ጎብኚዎችን በመሳብ ለሀገር ምጣኔ ሀብት አቅም በመሆን ላይ ይገኛል።

የያዝነው የካቲት ወር ደግሞ ከባለታሪኳ ኢትዮጵያ አልፎ በጥቁሮች ልብ ውስጥ የተጻፈና የሁሉም መኩሪያ የሆነ፣ ዓለምም በአድናቆት እንዲያያት ያስቻለ ገድል የተፈፀመበት ነው። በዚህም ወሩ የአፍሪካውያን ወር እስከ መባልም ደርሷል። የአፍሪካውያን ወር ያሰኘው ብቸኛው ምክንያትም ደግሞ የዓድዋ ድል ነው።

የዓድዋ ድልም እንዲሁ በተመሳሳይ በአኩሪ ታሪክ ተምሳሌትነቱ ከመወሳት ባለፈ የቱሪስት መስህብ ቢሆን የላቀ ድርሻ እንዳለው ተደጋግሞ የተነሳ ጉዳይ ነው። ወራቶቹ በታሪክ፣ በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና በፖለቲካዊ ጉዳዮች ሀገር የምታተርፍባቸው ናቸው።

በትውልድ ቅብብሎሽ ታሪክ እያስታወሰው፣ በተለያየ ዝግጅት የሚከበረው የካቲት 23 ቀን / የዓድዋ ድል በዓል እነሆ ዘንድሮም ለ127ኛ ጊዜ ይከበራል። እኔም በዚህ አጭር ጽሁፍ የዓድዋ ድል ለመዘከር /አንድ ለማለት ሞከርኩ እንጂ ጉዳዩ በዚህ ጽሁፍ «ዓባይን በጭልፋ» እንደሚባለው ሊሆንብኝ እንደሚችል አምናለሁ።

እነዛ በልማት ጊዜ ገበሬ፣ ሀገራቸው ስትደፈር ደግሞ ዳር ድንበሯን ለማስከበር ሞፈርና ቀንበራቸውን ሰቅለው ማቄን፣ጨርቄን፣ ልጄን፣ ሚስቴን ሳይሉ ሊያውም ዘመናዊ መሣሪያ ሳይታጠቁ በወኔ ከጠላት ጋር ተፋልመው ድል ስለተቀዳጁት፤ይህን ትውልድ አንገት ስላስቀኑ ወገኖች ጥቂት ማለት ፈለኩ።

ከዚህም ጎን ለጎን ዘመናዊ ኢትዮጵያን በመፍጠር፣ የአፍሪካና የመላው ዓለም ጥቁር ሕዝቦች የነፃነት ተጋድሎ መሪ እንደሆኑ የታሪክ ድርሳናት የሚመሰክሩላቸው ዳግማዊ አፄ ምኒልክን፣ ወቅቱንም ማስታወስ ወደድኩ።

ኢትዮጵያ ነፃነቷ ተከብሮ፣ ታፍራና ተከብራ እንድትኖር ጉልህ ስፍራ የነበራቸው አፄ ምኒልክ ብቻ አልነበሩም ባለቤታቸው እቴጌ ጣይቱም ነበሩ። ጦሩን ሰብቆ ኢትዮጵያን በኃይል ሊወር የመጣው ፋሽስት ጣሊያን በውጫሌ የውል ስምምነት ላይ ኢትዮጵያን ከጨዋታ ውጭ ሊያደርጋት የነበረውን ሴራውን በማክሸፍ እቴጌ ጣይቱ ጉልህ ሚና እንደነበራቸው ታሪክ ያስታውሳል።

የታሪክ ድርሳናት እንደሚያሳዩት የውጫሌ ውል አንቀጽ 17 የኢጣሊያንኛው «ኢትዮጵያ ከአውሮፓ መንግሥት ጋር ማድረግ የምትፈልገውን ግንኙነት በጣሊያን መንግሥት በኩል ማድረግ አለባት» የሚል ሲሆን፣ በአማርኛው ደግሞ «ኢትዮጵያ ከአውሮፓ መንግሥት ጋር ማድረግ የምትፈልገውን ግንኙነት በጣሊያን መንግሥት በኩል ማድረግ ትችላለች»

በሁለቱ ቋንቋዎች በውሉ ላይ የተገለፀው ሰፊ የትርጉም ልዩነት እንዳለውና የጣሊያንኛው ትርጉም የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት የሚዳፈር ብቻ ሳይሆን፣ ብሄራዊ ክብሯን የሚያስደፍርና ጥቅሟንም አሳልፎ የሚሰጥ እንደሆነ የተገነዘቡት የኢትዮጵያ መሪ፣ውሉ የኢትዮጵያን ክብር በሚያስከብርና ጥቅሟንም አሳልፎ በማይሰጥ መልኩ መልሶ እንዲስተካከል በተደጋጋሚ ቢያቀርብም ስምምነት ላይ አለመደረሱን ታሪክ ያስረዳል።

ይሄኔ ነገሩ ያላማራቸው ብልህዋ እቴጌ ጣይቱ በአንቀጹ ላይ የሰፈረው ጽሁፍ አደገኛነትና ከወራሪው ጋር ጦርነት መግጠም እንደሚያስፈለግ ለአፄ ምኒልክ እንደነገሯቸው ታሪክ ያመለክታል። ሀገራዊ ክብርና ጥቅም ሲነካ፣ ክብሯን ማስጠበቅ ከአንድ ሀገር መሪ የሚጠበቅ ብቻ ሳይሆን፣ ኃላፊነትና ግዴታም በመሆኑ ወራሪውን ፋሽስት ጣሊያንን በመጣበት መክቶ ለመመለስ ህዝቡ ለዘመቻ እንዲዘጋጅ ጥሪ አቅርበዋል።

> እነዛ በልማት ጊዜ ገበሬ፣ ሀገራቸው ስትደፈር ደግሞ ዳር ድንበሯን ስማስከበር ሞፈርና ቀንበራቸውን ሰቅለው ማቄን፣ጨርቄን፣ ልጄን፣ ሚስቴን ሳይሉ ሲያውም ዘመናዊ መሣሪያ ሳይታጠቁ በወኔ ከጠላት ጋር ተፋልመው ድል ስለተቀዳጁት፤ ይህን ትውልድ አንገት ስላስቀኑ ወገኖች ጥቂት ማለት ፈለኩ

የክብር ጉዳይ ነውና የክተት ዘመቻ ጥሪውን ለመቀላቀል ወደኋላ ያለ እንዳልነበር ጦርነቱና የተገኘው ድል ምስክር ነው። ከታሪክ ድርሳናት የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው ከፋሽስት ጣሊያን ጋር ዓድዋ ላይ የተደረገው ጦርነት ከአራትና አምስት ሰዓታት በላይ አልዘለቀም። በአየርና በየብስ ዘመናዊ መሣሪያ የታጠቀውን ወራሪ ኃይል ሙትና ቁስለኛ ከማድረግ ባለፈም የጦር አዛዦችን፣ ቁጥር ስፍር የሌለው መሣሪያዎችንና መድፎችን በመማረክ ጀብድ በመፈጸም በጠላት ላይ ድል የተቀዳጀው ኢትዮጵያዊ የማረካቸውን የጦር መሣሪያዎች በአጋሰስ ጭኖ ወደ አዲስ አበባ ሲመለስም ውሎ አላደረም።

ለጦርነቱ መነሻ የሆነው የውጫሌ ውል ስምምነት ፋሽስት ጣሊያንን ዋጋ ያስከፈለና ለውርደትም የዳረገ፣ ኢትዮጵያን ደግሞ ዳር ድንበሯን አናስደፍርም ብለው ከቀፎው እንደወጣ የንብ መንጋ በአንድ ሆነው ባደረጉት ተጋድሎ ያስመዘገቡት ድል በመላው ዓለም ስሟ እንዲጠራ አድርጓል።

በባዶ እግር፣ በመድፍ ታግዞ ዘመናዊ መሣሪያ ከታጠቀ ኃይል ጋር ተዋግቶ ያሸነፈ እስካሁን በታሪክ አልተሰማም። ለዚህም ነው የዓድዋ የድል በዓል በየአመቱ እንደ አዲስ የሚወሳው፣ ታሪኩም ገና የሚነገረውና አይረሴ የሆነው። ድሉና ታሪኩ ኢትዮጵያውያንን ብቻ ሳይሆን፣ የውጭ ጸሐፍትንም አነሳስቷል።

በዓድዋ ድል ማግሥት የዓለም ታሪክ ተገለበጠ፣ ታላቅ የትውልድ ኃይል በአፍሪካ ተቀሰቀሰ ብለው የዘገቡትን የእንግሊዝ ጋዜጦች በታሪክ እናገኛለን። ታላቁ የጥቁር ህዝቦች ድል (ዓድዋ ድል)በመላው ዓለም ፖለቲካ ላይ ለውጥ በማምጣትም ሚናው የጎላ እንደሆነም ታላላቅ ፀሐፍት በብእራቸው ማስፈራቸው ይታወቃል።

ጋዜጠኛና ደራሲ ጳውሎስ ኞኞ የኢጣሊያንና የኢትዮጵያ ጦርነት በሚለው መጽሐፉ ላይ እንደገለጸው የዓድዋ ድል በዓል ለመጀመሪያ ጊዜ የተከበረው በ1895 ዓ.ም ሲሆን፣ በዓሉም አሁን በሚከበርበት ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ምኒልክ አደባባይ ነው። በወቅቱም በነቂስ ከወጣው ኢትዮጵያዊ በተጨማሪ ዲፕሎማቶች ታድመዋል። የፈረሰኞቹ ብዛትም ልክ አልነበረውም።

የዓድዋ ድል የአንድ ወቅት ብቻ አይደለም። ጽናት፣ አንድነት፣ መከባበር፣ የሀገር ፍቅር ስሜት የምንማርበት ተምሳሌት ነው። በመሆኑም አኩሪ ድሉን ስናጣጥም ያለብንንም ኃላፊነት ሳንዘነጋ መሆን ይኖርበታል። በጀግኖች አባቶች አጥንትና ደም ታፍራና ተከብራ የቆየችውን ኢትዮጵያን ከውጭ ጠላት ጠብቆ፣ በውስጥም አንድነትን፣ አብሮነትን፣ መከባበርን አጠናክሮ በጋራ የመኖር እሴትን ማቆየትና ለተተኪ ትውልድ የማሸጋገር ኃላፊነት የዚህ ትውልድ መሆኑ መዘንጋት የለበትም።

ይህን ማድረግ ካልቻልን የውጭ ጠላቶች በቀላሉ በተከፈተላቸው በር ገብተው አንድነታችንን እንዲንዱ እድል ይመቻችላቸዋል። በዚህ ደግሞ የምናጣው ሀገራችንን ብቻ ሳይሆን እስከዛሬ አንገታችንን አቅንተን የምንጓዝበትን ነፃነታችንን ጭምር ነው ፤ መልካም የዓድዋ ድል በዓል።

# 36ኛው የአፍሪካ ሕብረት የመሪዎች ጉባኤ

ግርማ መንግስቴ

"የአፍሪካ አህጉራዊ ነፃ የንግድ ቀጣና መቀላጠፍ" በሚል መሪ ሃሳብ በአዲስ አበባ የተካሄደው የዘንድሮው የአፍሪካ ሕብረት የመሪዎች ጉባዔ እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ2019 ወደ ሥራ የገባውንና 1 ነጥብ 4 ቢሊየን ያህሉን የአሕጉሪቱን ሕዝብ በንግድ ለማስተሳሰር የታለመውን የንግድ ቀጣና ይበልጥ ተግባራዊ ማድረግ በሚቻልበት ጉዳይ ላይ መክሯል።

በተለይም የጋራ የጉምሩክ ሥርዓትና ወጥ የታሪፍ አስተዳደር በአሕጉሪቷ ለመተግበር ትኩረት እንዲደረግበት፣ የእርስ በርስ የንግድ ግንኙነትን የሚያቀጭጩ አሰራሮች መሻሻል እንደሚገባቸውና የተሳለጠ የንግድ ሥርዓት ለመፍጠር ሀገራት ትኩረት እንዲሰጡ መክሯል፤ በአፍሪካ በአየር ንብረት ለውጥ የተከሰቱ የድርቅና ረሃብ ጉዳቶችን እንዲሁም በዩክሬንና በሩስያ ጦርነት ምክንያት አደጋ ላይ የወደቀውን የአሕጉሪቱን የምግብ ዋስትና ችግር በተመለከተ ምክክር አድርጓል።

የአፍሪካ የ2063 አጀንዳ አፈጻጸም፣ ባለፉት ጥቂት ዓመታት በአፍሪካ ሰላምና ደኅንነት ለማረጋገጥ እንዲሁም የተሻለች አፍሪካን ለመገንባት የተቀመጠውን የረዥም ጊዜ ዕቅድ አፈጻጸም ላይም የኮሚሽኑን ሥራዎች ሪፖርት ተመልክቷል።


ፎቶ - ኢዮብ ተፈራ

## በጉባኤው እነማን ተገኙ?

በመረጃዎች እንደሚያመለክተው በጉባኤው፤ የ35 የሀገራት መሪዎች (ፕሬዝደንቶች እና አራት ጠቅላይ ሚኒስትሮች)፣ 11 የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች፣ 13 ቀዳማዊ እመቤቶችና 10 የዓለም አቀፍ ድርጅት ኃላፊዎች ታድመዋል።

በጥቅሉ 852 ጋዜጠኞች (332ቱ የሀገር ውስጥ እንዲሁም 70ዎቹ ተቀማጭነታቸውን ኢትዮጵያ ያደረጉ የውጭ ሀገራት መገናኛ ብዙኃን የዜና ወኪሎች) 450ዎቹ ደግሞ ከተለያዩ ሀገራት የመጡ የውጭ ሀገራት መገናኛ ብዙኃን ጊዜያዊ የዜና ወኪሎች ጉባኤውን ለመዘገብ በኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለስልጣን ፈቃድ አግኝተው ጉባኤውን ዘግበዋል።

## በጉባኤው መሪዎች ምን አሉ?

### * የሲኔጋል ፕሬዚዳንት ማኪ ሳል/የቀድሞው አፍሪካ ህብረት ሲቀመንበር/

ባለፈው ጉባኤ አፍሪካ የቡድን 20 አባል ሀገራት ሙሉ አባል ለመሆን ጥያቄ እንደታቀረብ በተሰጠው አቅጣጫ መሰረት ያቀረበችው ጥያቄ በጥሩ ሂደት ላይ መሆኑን ገልጸዋል።

አህጉሪቷ በሽብርተኝነት፣ የአየር ንብረት ለውጥ፣ የእርስ በእርስ ግጭትና ሌሎችም የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ችግሮች እየተፈተነች ነው ፤ በመሆኑም በምጣኔ ሀብት የበለጸገች፣ ሰላም የሰፈነባትና የምንመኛትን ጠንካራ አፍሪካን ዕውን ለማድረግ ከዓለም መንግስታትና በአሕጉሪቱ ያለውን የእርስ በርስ ትብብር ማጠናከር ይገባል ብለዋል።

በአውሮፓ ሕብረት፣ የቡድን 7 አባል አገራት እና መሰል ስብሰባዎች ላይ ከአፍሪካ ጋር የትብብር ግንኙነቶች እንዲጠናከሩ የማድረግ ፍላጎት መኖሩን ጠቁመዋል። አሕጉሪቷ ከዓለም መንግስታት ጋር ያላትን ግንኙነት በማጠናከር በኩል የተለያዩ ስራዎች መከናወናቸውን አስታውቀዋል። በዓለም ምጣኔ ሃብትና የፋይናንስ ስርአት ፍትሃዊነት ጉዳይ እንዲሁም የቡድን 20 አባል ሀገራት ሙሉ አባል ለመሆን አፍሪካ ያቀረበችው ጥያቄ በመልካም ሂደት ላይ መሆኑን አስታውቀዋል።

በአሁኑ ወቅት ሩስያ፣ አሜሪካ፣ ፈረንሳይ፣ ደቡብ አፍሪካ እና ቻይናን ጨምሮ ከ20 በላይ የቡድን 20 አባል አገራት ድጋፋቸውን መግለጻቸውንም ያብራሩት ማኪሳል፤ ሌሎች አባል ሀገራትም ይህንን ድጋፍ በመቀላቀል በቀጣይ በህንድ በሚካሄደው የአባል ሀገራቱ ስብሰባ ላይ አፍሪካ የቡድን 20 አባልነት ዕውን ይሆናል የሚል ግምት እንዳላቸው ገልጸዋል።

በአሕጉሪቱ የምጣኔ ሃብት መነቃቃትን ለማምጣት የተፈጥሮ ሃብትን በመጠቀም ለዓለም ገበያ በተወዳዳሪ ዋጋ ማቅረብ እንደሚያስፈልግ፤ በተለይም በአሕጉሪቱ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ማግኘት ላልቻሉ ከ600 ሚሊዮን በላይ ዜጎች የኃይል አቅርቦት ዕውን ማድረግም ጊዜ ሊሰጠው አይገባም ብለዋል። የአፍሪካ ምጣኔ ሃብት የሚያስፈልገውን ያህል የፋይናንስ አቅርቦትና ድጋፍ እያገኘ ባለመሆኑ የፋይናንስ ድጋፍና አማራጭን ማጠናከር እንደሚገባ አሳስበዋል።





### * ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ አሕመድ

"በተመድ የጸጥታው ምክር ቤት አፍሪካ ቋሚ መቀመጫ ይገባታል"፤ እንዲሁም "ለአፍሪካ ትክክለኛና ሚዛናዊ መረጃ የሚያቀርብላት የአፍሪካ ህብረት አሕጉራዊ ሚዲያ ያስፈልጋል ብለዋል።

ባለፉት ዓመታት ኢትዮጵያ በገጠማት ችግር ዓለም አቀፍ ሚዲያዎች የተሳሳተ መረጃ ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ሲያደርሱ ቆይተዋል፤ ይህን አይነቱን ችግር ለዘለቄታው ለመቋቋም ለአፍሪካ ትክክለኛና ሚዛናዊ መረጃ የሚያቀርብላት የአፍሪካ ሕብረት አሕጉራዊ ሚዲያ መቋቋም እንደሚያስፈልግ አመልክተዋል።

"አፍሪካዊ ችግሮችን አፍሪካዊ መፍትሔ" በሚል መርህ ከሁለት ዓመት በፊት በኢትዮጵያ ሰሜኑ ክፍል የተከሰተውን ጦርነት ለማቆም ኢትዮጵያ አፍሪካዊ መፍትሄን አግኝታለች፤ በዚህም አፍሪካ ችግሮችን በሰላማዊ መንገድ እየፈታች ለመሆኑ ማሳያ ነው"ብለዋል። የሰሜኑ ጦርነት እንዲቆም የአፍሪካ ሕብረት ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጓል" ሲሉ ምስጋና አቅርበዋል። አፍሪካ ብዙ ችግሮች አሉባት፣ ያለ ውጭ ጣልቃ ገብነት እነዚህን መፍታት የሚቻለው በውይይት በትብብር መስራት ሲቻል እንደሆነም ጠቁመዋል።

"ኢትዮጵያ ባለፉት አራት ዓመታት በአረንጓዴ አሻራና በበጋ መስኖ በምግብ ራሷን ለመቻል ውጤታማ ስራ ሰርታለች"፤ ከ25 ቢሊዮን በላይ ችግኞችን በመትከል የአየር ንብረትን ለመቋቋም የሚያስችል አቅም ገንብታለች። በምግብ ራሷን ለመቻል ባደረገችው ጥረት የበጋ የስንዴ መስኖ በመዝራት ከራሷ አልፋ ወደ ውጭ መላክ ጀምራለች" ብለዋል።

### * የአፍሪካ ሕብረት ኮሚሽን ሲቀመንበር ሙሳ ፋቂ መሃመት

የአፍሪካ ሕብረት ሁሉንም አባል ሀገራት ማዕከል ያደረገና የጋራ ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጥ እንዲሆን እየሰራን እንገኛለን። በዓለም የሚታየውን የተዛባ አመለካከትና የመንግስታት አስተዳደር ለማስተካከል አሁንም ድምጻችንን ማሰማት መቀጠል ይገባል ፤ አፍሪካን ከተባበሩት መንግስታት ድርጅት የጸጥታው ምክር ቤት ማግለል ኢፍትሃዊ ውሳኔ ነው ብለዋል።

በአሕጉሪቱ የሚታዩ የፖለቲካና የደህንነት ችግሮች አሁንም ፈተና ሆነው መቀጠላቸውን በመጥቀስ ህገ መንግስታዊ ስርዓት በጣሰ መልኩ የሚደረጉ የመንግስታት ለውጦች ሀገራትን የመበታተን አደጋ እንደደቀነባቸውም አመልክተዋል።

ሽብርተኝነትና ከምርጫ ውጭ ስልጣን ለመያዝ የሚደረግ ጥረትና የአየር ጸባይ ለውጥ አሁንም የአጉሪቱ ችግሮች ሆነው መቀጠላቸውን፤ በአሕጉሪቱ ህገ መንግስትን በጣሰ መልኩ ስልጣን የሚወጡ ኃይሎች ላይ



የሚጣሉ ማዕቀቦች ውጤት ከማስገኘት ይልቅ ህዝብን ለችግር መዳረጋቸውን አስታውሰዋል። በመሆኑም ማዕቀቡ የሀገራትን ኢኮኖሚ የሚያንኮታኩትና ከፍተኛ ተጽዕኖ የሚያሳድር መሆኑን በመገንዘብ አማራጭ የመፍትሄ እርምጃ ማስቀመጥ እንደሚገባ አሳስበዋል።

"አፍሪካን በ2030 የጥይት ድምጽ የማይሰማባት አሕጉር" ለማድረግ የተጀመሩ ጥረቶች ግባቸውን እንዲመቱ ሕብረቱ ከፍተኛ ገንዘብ በመመደብ እየተንቀሳቀሰ ነው፤ "የተደቀኑ ችግሮችንና ይዘዋቸው ሊመጡ የሚችሉ ፈተናዎችን ቀድመን በመገንዘብ በጋራ ልናልፋቸው ይገባል" ብለዋል።

የአፍሪካ ሀገራት የኢኮኖሚ ዕድገት ባለፉት ሶስት ዓመታት በገጠሙት ዘርፈ ብዙ ችግሮች በነበረበት መቀጠል አልቻለም ያሉት ሙሳ ፋኪ፣ "የዋጋ ግሽበቱ ከሚጠበቀው በላይ ማሻቀብ፣ የነዳጅ ዋጋ መጨመርና ግጭት የአሕጉሪቱ ሳንካዎች ሆነው ቀጥለዋል፤ ይህ ደግሞ የሀገራትን ኢኮኖሚ የሚያንኮታኩትና አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድር መሆኑን በመገንዘብ አማራጭ የመፍትሄ እርምጃ ማስቀመጥ እንደሚገባ አመልክተዋል።



### * የተመድ ዋና ጸሐፊ አንቶኒዮ ጉተሬዝ

"አፍሪካ አፍሪካ እምቅ የሆነ የመልማት አቅም አላት። ይህን አቅም ለማልማትና ያሉባትን ችግሮች ለመፍታት በምታደርገው ጥረት የተባበሩት መንግስታት ድጋፍ ያደርጋል፤ "ነጻ የንግድ ቀጠናን ማሳለጥ ለስራ እድል ፈጠራ ወሳኝ በመሆኑ አፍሪካ በ2060 ለያዘችው የግብ አጀንዳ ያላትን ሀብት በአግባቡ በመጠቀም ህዝቡ ያለበትን ችግር በመፍታት የተሻለ እድገት ማስመዝገብ ተገቢ ነው" ብለዋል። "ለዚህ ግብ ስኬት ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማት እገዛ ማድረግ እንዳለባቸው አመልክተዋል።

የዓለም የፋይናንስ ስርዓት ፍትሃዊ በሆነ መልኩ ለአፍሪካና አጠቃላይ በማደግ ላይ ላሉ ሀገሮች በሚጠቅም መልኩ መቃኘት ይኖርበታል፤ ዓለምን እየፈተነ ላለው የአየር ንብረት ለውጥ ችግርም ዕልባት ለማበጀት የጋራ ጥረት ማድረግ እንደሚገባ አሳስበዋል። ለዚህ ደግሞ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የአፍሪካን የልማት እቅዶች በመደገፍ በአሕጉሪቱ ዘላቂ ሰላምና ቀጣይነት ያለው ዕድገት ዕውን እንዲሆን ድጋፉን እንደሚቀጥል አረጋግጠዋል።

### * አዛሊ አሱማኒ/የኮሞሮሱ ፕሬዚዳንት የወቅቱ የአፍሪካ ሕብረት ሲቀመንበር /

"የአፍሪካ አገራትን የብድር ጫና ለማቃለል አበዳሪ አገራትና ዓለም አቀፍ የገንዘብ ተቋማት የጋራ የብድር ማቅለያ ማዕቀፍ በማበጀት ሊሰሩ ይገባል" ብለዋል።

ባለፈው የፈረንጆች ዓመት የኮቪድ 19 ወረርሺኝ እና የዩክሬንና የራሺያ ጦርነት በዓለም አቀፍ ደረጃም ሆነ በአፍሪካ ከባድ ተጽዕኖ ማሳደሩን፤ ይህንንም ተከትሎ የአፍሪካ አጠቃላይ እድገት ከሦስት በመቶ እንዳይልቅ ማድረጉን በመጥቀስ በአንጻሩ የአህጉሪቱ የውልደት መጠን ከፍተኛ መሆኑ አሉታዊ ጫና አሳድሯል ብለዋል።

በተለይም የአህጉሪቱን የማኅበራዊና መሰረተ-ልማት በተፈለገው ደረጃ እንዳያድግ በማድረግ 22 የሕብረቱ ሀገራት የብድር ጫና ውስጥ ስለመሆናቸው የዓለም ባንክን መረጃ የጠቀሱት አዲሱ የሕብረቱ መሪ፣ እነዚህ አገራት ዕዳቸውን ለመክፈል ስለሚያዳግታቸው የብድር ጫናውን ለማቃለል አበዳሪ ሀገራትና ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማት የጋራ የብድር ማቅለያ ማዕቀፍ ሊያዘጋጁላቸው እንደሚገባ ጠቁመዋል። "ምዕራባውያን ከወራት በፊት ለአፍሪካ የኢኮኖሚ ማገገሚያ የሚውል 150 ቢሊየን ዩሮ ለመስጠት የገቡትን ቃል በመጠበቅ ገንዘቡን በፍጥነት መልቀቅ እንዳለባቸው አሳስበዋል።

"የዩክሬንና የሩስያ ጦርነት አፍሪካ ራሷን መቻል እንዳለባት አሳይቶናል" ያሉት አዛሊ፤ በተለይም የግብርና ዘርፉን ማጠናከር ወሳኝ መሆኑን አስታውቀዋል። በአሕጉሪቱ የምጣኔ ሃብትና ጠንካራ የፖለቲካ ሥርዓት ግንባታ ውስጥ የሴቶችን ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማሳደግ በእሳቸው የአመራር ዘመን ቅድሚያ የሚሰጠው ሥራ እንደሚሆንም ገልጸዋል። በአፍሪካ ሀገራትና አጋር አካላት እንዲሁም ከሌሎች አቻ ተቋማት ጋር ያለውን ትብብር በማጠናከር አህጉሪቱን ወደ ተሻለ ምዕራፍ ለማሻገር በሊቀ-መንበርነት ጊዜያቸው የሚሰሩ መሆኑንም አረጋግጠዋል።

ማህበራዊ

# ሀገርኛ

# አጉማስ

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

ባህል ሰፊና ጥልቅ የሆኑ የአንድ ማህበረሰብ እውቀቶችን፣ እምነቶችን፣ ኪነ-ጥበቦችን፣ ህጎችን፣ ልማዶችን፣ ወዘተ ... ያካተተ በህብረተሰቡ ዘንድ ለረጅም ዘመናት ሲከናወን የነበረ በህብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያለውና በህበረተሰቡ የተፈጠረና የሚያድግ ነው። ባህል የማንነት መገለጫ አስተሳሰብና ባህርይ ሆኖ አንደኛው ከሌሎች የሚማሩበት፣ የሚያዋህዱት ለቀጣይ ትውልድም የሚያስተላልፉት ነው።

ባህል ውርርስ፣ ሽግግር፣ ትውውቅም ነው። ውርርስ ሲባል ደግሞ መቅዳት እና ማስቀዳት ያለበት ነው። ለምሳሌ፡- አንድ ሰው ከአፍ መፍቻ ቋንቋው በተጨማሪ ሌሎች ቋንቋዎችን ሲማር ወይም መናገር ሲጀምር የቋንቋ እውቀቱን ብቻ ሳይሆን ባህሉንም አብሮ ይቀዳል። እውቀት እና ከእውቀት የሚመነጩ ሀሳቦችንም ጭምር ይማራል። ያ ማህበረሰብ ምን ይፈልጋል፣ ምን ይጠላል የሚለውን ጭምር ይለያል። ባህል ማለት ከአንዱ መውሰድ ለሌላው መስጠት ያለበት፤ የተሰጠውም ለሌላ ማቀበልም ነው። ለመሆኑ ስለባህል ይህንን ያህል ለምን አነሳን ከተባለ ዛሬ ልናነሳው የወደድነው ጉዳይ ባህልን በብዙ ትርጉሙ የሚያሳየን ስለሆነ ነው።

ጉዳዩ ወደ ሰሜኑ ክፍል ጎራ ብለን ያገኘነው ሲሆን፤ ዘመናትን በማህበረሰቡ የኖረና አሁንም ያለ ነው። ታሪክም ባህልም ሆኗቸው ይኖሩበታል። ለልጅ ልጃቸውም እያስተላለፉት ማህበራዊ ትስስራቸውን፣ ኢኮኖሚያዊ ክፍታቸውን ይገነቡበታል። ፖለቲካውን ጭምር ዲሞክራሲ ያደረጉበት መርሃቸው ሆኖላቸዋል። « አጉማስ » እያሉ የሚጠሩት ባህላቸውን። በተለይም በአርሶ አደሩ አካባቢ በብዛት የሚተገበርና የሚኖርበት ሲሆን፤ ከአዲስ ሰብል ስብሰባ ጋር በስፋት ያነሱታል። ይተገበሩታልም።

ይህንን ባህላዊ ትውፊት ኑሯቸው ካደረጉት መካከልም አርሶ አደር ወልዴ ያለው አንዱ ናቸው። በአማራ ክልል ደቡብ ጎንደር ዞን በፎገራ ወረዳ ወርቅደሞ ቀበሌ ውስጥ ይኖራሉ። ይህንን ባህል ከልጅነታቸው ጀምሮ ያውቁታል። አሁን ደግሞ ራሳቸውም ደጋሽና አጉራሽ ሆነው ለልጆቻቸው እያስተማሩትም፤ እያወረሱትም ይገኛሉ።

እንደ እርሳቸው አባባል፤ አጉማስ ማለት የውድማ ረድኤት፣ በረከት ማለት ነው። እህሉ ደርሶ በደቦ ሲወቃ አለያም ሲሰበሰብ የደከሙ አካላት እንስሳቱን ጨምሮ አርፈው የሚመገቡት ስርዓትም ነው። ከዚያ ሻገር ሲልም አጉማስ የድግሱ ስያሜ ይሆናል። ማለትም እናቶች ምግብና መጠጡን ሲያዘጋጁ « ለአጉማስ የሚሆን ምግብ እያዘጋጀሁ ነው» ይላሉ። ይህ ምግብ ቅድሚያ ከደረሰው እህል አለያም ከነባሩ እህል መዘጋጀት ይችላል። ጤፍን ግን አይነካም። ምክንያቱም በመጨረሻ የሚደርስ እህል ስለሆነ ለድግሱ አይደርስም። የመሰባሰቢያውና አብሮ የመመገቡ መንስኤም እርሱ እንደሆነ በስፋት ይወሳል።

አጉማስ ሌላም ትርጉም አለው። ይህም እህሉን ከእብቁ የሚለየው ንፋስ ሲሆን፤ አጉማስ መጣች በማለት ማህበረሰቡ ፈጥኖ ወደስራው የሚገባበት አቅጣጫ ጠቋሚና አመላካች ሲሳይ ተደርጎ ይወሰዳልም። ስለዚህም አጉማስ ማለት እንደ አርሶ አደር ወልዴ ገለጻ፤ ሲሳይ፣ ጸጋ፣ ሀብት፣ በረከት እንደማለት ነው። ታዲያ ይህ ድግስ ምን ይጠቅማል? ከተባለ አሁንም አርሶ አደሩ እንዲህ ያብራሩታል።

የመጀመሪያው ሁሉም የሚያርፍበትና በጋራ የሚመገብበት ሲሆን፤ ማህበራዊ ትስስርን ለማጠናከር ሁነኛ መፍትሄን ይሰጣል። ምክንያቱም በመሰባሰቡ ውስጥ የትናንቱን እያወሳ የዛሬን፣ የነገንና የሚመጣውን እቅዱን ያዘጋጃል። ማን ምን ማድረግ እንዳለበት የሥራ ድርሻን ይከፋፈላል። ከዚያ ሻገር ሲልም የድግሱ ተሳታፊ ሥራ ላይ ተሰማርቶ የነበረው ብቻ ሳይሆን አላፊ አግዳሚውም በመሆኑ ዝምድናን ይፈጥራል። ማለትም በአጉማስ ቅምሻ አበልጅነት ይመጣል። መሃን የሆኑ ጥንዶች ባይወልዱም በድግሱ የተደሰቱ ተሳታፊ እናቶች ወይም አባቶች ለደጋሹ ዝምድናቸውን ለማጠንከር ሲሉ ልጃቸውን በአበልጅነት ይሰጡታል።



**አጉማስ የእርቅ ማዕድም ነው። እርቅና ሰላም ይሰፍናል። ደም የተቃባ ሳይቀር ይቅር ይባባልበታል። ምክንያቱም ለአጉማስ የተዘጋጀውን ምግብ ሁሉም መቋደስ ግዴታው ነው። የተጣላ ጎረቤት እንኳን ይህንን ድግስ ማለፍ አይችልም። ካለፈ የእርሱን የሚበላለት የለም። ስለዚህም በድግሱ ተሳትፎ በልቶና ጠጥቶ መርቆ መንገዱን ይቀጥላል። የተጣላውም ሰው ቢሆን አይቶት ዝም አይልም**

ከዚያ ባሻገር በኑሮ ዝቅተኛ የሆኑ ወላጆች ከአጋጠሙም አሳድገው ብለው እስከመስጠት ይደርሳሉ።

ይህ አጋጣሚ ደግሞ በስፋት የሚታየውና የሚፈጠረው ለመውለድ የተቃረበች ሴት ወደ ጤና ጣቢያ በምትሄድበት ጊዜ እንዳይሸታት ተብሎ ከምግቡ እንድትቀምስ ስትደረግና ወልዳ ስትመጣ በእንክብካቤ ሲቀበሏት አለያም ደግሞ እዚያው ድግሱ ቤት ስትወልድ ነው። ይህም በአካባቢያቸው በተደጋጋሚ እንደተከሰተ ያነሳሉ። እርሳቸው ጭምር በዚህ አይነት ሁኔታ ዘመድ እንዳፈሩ ይናገራሉ።

ሌላው በአጉማስ ድግስ የሚፈጠረው «ልጅህን ለልጄ» የሚለው አይነት የጋብቻ ዝምድና ሲሆን፤ ተግባሩ የሚፈጸመው ግን እንደ ልጆቹ ፈቃደኝነት ነው። ቤተሰቡ የወደደውን ልጆቹ ከተቀበሉት ቤተሰባዊ ዝምድናን ይፈጥሩበታልና አጉማስ ዘር ማብዢያ፣ ቤተሰብ መፍጠሪያ ነው ይላሉ አርሶ አደሩ ወልዴ።

አጉማስ ሰው የማይለይበት ሁሉም በሕብረት የሚቋደስበት ሲሆን፤ ደጋሹ እህሉ በረከት እንዲያገኝ አላፊ አግዳሚውን ብሉልኝ ጠጡልኝ የሚልበት ነው። ያንን የተመገበ ሁሉ ምላሹ ገንዘብ አለያም ሌላ ነገር ሳይሆን ምርቃት ብቻ ነው።

አጉማስ በደቦ የሚከወን ስለሆነ ለቀን ሰራተኛ የሚወጣውን ከፍተኛ ገንዘብ ይቆጥባል። ለማጓጓዣ የሚወጣውንም ወጪ እንዲሁ ይቀንሳል። ምክንያቱም የአካባቢው ጋማ ከብት በሙሉ ተሰብስቦ እህሉን ወደጎተራው እንዲያስገባ ያደርገዋል። አጉማስ ሰዓትም ቢሆን ቆጣቢ ነው። በአጭር ጊዜ ስራውን አከናውኖ ሌላ ስራ ላይ ሰውዬው እንዲሰማራ ያደርገዋል።

አጉማስ የእርቅ ማዕድም ነው። እርቅና ሰላም ይሰፍናል። ደም የተቃባ ሳይቀር ይቅር ይባባልበታል። ምክንያቱም ለአጉማስ የተዘጋጀውን ምግብ ሁሉም መቋደስ ግዴታው ነው። የተጣላ ጎረቤት እንኳን ይህንን ድግስ ማለፍ አይችልም። ካለፈ የእርሱን የሚበላለት የለም። ስለዚህም በድግሱ ተሳትፎ በልቶና ጠጥቶ መርቆ መንገዱን ይቀጥላል። የተጣላውም ሰው ቢሆን አይቶት ዝም አይልም። ይህንን ካደረገ በረከቱ እንደሚነጠቅበት ያውቃል። እናም በረከቴን እንዳታሳጣኝ ሲል ቅመስልኝ ይላል። እናም በአጉማስ ድግስ መቃቃር ሳይሆን መቀራረብ ብቻ ይጎላል። ተሰባስቦ መብላትም ልዩ ቦታ ይሰጠዋል።

ሌላው የአጉማስ ፋይዳ አብሮ ከመብላት ጋር ያለው መልካም ዝምድና ሲሆን፤ ጠብን እስከማብረድ የሚደርስበት ነው። «አብሮ የበላ ቅዱስ ዮሐንስ አይሸረውም» እንደሚባለው ምንም ነገር አዲስ ሆኖ ቢመጣ አብሮ የበላን ሰው ሊለውጠው የሚችለው ነገር የለም። አጉማስ ደግሞ አብሮ መብላትና አብሮ መስራት ነው። ስለዚህም ወንድማማችነት ይጠነክርበታል እንጂ መለያየት አይሰፍንበትም። ለፍቅር እንጂ ለመጥፎ ነገር እንዳይተሳሰብ የማድረጊያ መንገድ ነው።

ሳይንስን ወይም ሃይማኖትን መነሻ ያደረጉና ለህብረተሰቡ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ባህላዊ እሴቶች መልካም ዋጋ ያላቸው ልማዳዊ ድርጊቶች ከሚባሉት መካከል አንዱ አጉማስ እንደሆነ የነገረን ደግሞ ቤተሰቦቹ ስሙን አጉማሴ ብለው የጠሩት እንግዳችን ነው። እነርሱ እንደሚለው፤ አጉማስ ለሀገርና ህዝብ ደህንነት፣ ብልፅግናና ማህበራዊ ትስስር ዋነኛና አስፈላጊ ባህል ነው። የአጉማሱን ምግብ የቀመሰ ሁሉ በአስተሳሰብ የቀና፣ አገሩን የሚወድና መልካም ባህሎቻችንን ይዞ ለልጅ ልጁ የሚያስተላልፍ ነው። በባህሉ የሚኮራም ነው።

የአጉማስ ድግስ ጊዜ የማያርፍ ነገር የለም። ሁሉም ድካማቸውን እንዲረሱ ይደረጋሉ። እንስሳት ሳይቀሩ ልክ እንደሰው ሁሉ እየበሉ እንዲቦርቁና እረፍት እንዲያገኙ ይደረጋሉ። ምክንያቱም በደቦው እህል ሲያደርሱ፣ ሲወቁ ቆይተዋል። እናም አጉማስ የእንስሳትን እረፍት አስፈላጊነት የሚያሳይ ባህል ነው። በተጨማሪም አጉማስ የራበው ሰው የሚመገብበት ነው። ምክንያቱም መንገደኛው በጉዞ ደክሞት አረፍ የሚልበት ነው። ገንዘብ ሳያወጣ ረሀቡን አስታግሶ ፀሐይን አሳልፎ መንገዱን የሚቀጥልበት ነውና።

ነደያንም በዚህ ግብዣ ላይ እንደማንኛውም ሰው እስከፈለጋቸው ድረስ እንዲመገቡና እንዲጠጡ ይፈቀድላቸዋል። ምክንያቱም የአጉማስ ድግስ በረከትና ደስታ መፈለጊያ ነው። በጣም የሚገርመው በአጉማስ ድግስ ሰርገኛ ጭምር ይጋበዛል። በአካባቢው ላይ የሚያልፍ ከሆነ ያንን ረግጦ መሄድ አይችልም። ገብቶ ተመግቦና ጠጥቶ መርቆ የመሄድ ግዴታ አለበት።

በአጉማስ የሚሰበሰበው ምርቱ ብቻ አይደለም። ሰውም እንስሳትም ጭምር ነው። ምክንያቱም አንድ ሰው ጤፉን መውቃት ሲያስብ ሊኖረው የሚችለው በዛ ከተባለ ሁለት በሬ ነውና በደቦ ሲሰራ ደግሞ ይህ ብቻ በቂ ስለማይሆን ከአካባቢው ሰው ከብቶችን በመበደር አምጥቶ ይወቃል። ምርቱን ወደቤቱ ሲያስገባም እንዲሁ እንስሳቱን ከየጎረቤቱ ሰብስቦ ነው። በተጨማሪም ውቂያውን ሲያደርግ በህብረት ማለትም በደቦ ሰዎች ተሰብስበው ነው። እናም በመሰባሰብ ውስጥ ያለውን ፋይዳ ያሳያል።

አጉማስ የጎረቤትን ንብረት እንደራስ የመጠቀም ዕድልን ይፈጥራል። ምክንያቱም በአካባቢው አጉማስ ደጋሹ ማን እንደሆነ ይታወቃልና እርሱ ሰብስቦ ወስዷቸው ይሆናል ነው የሚባለው እንጂ ለምን የእኔን የጋማ ከብት ነካህ ብሎ ነገር የለም። እናም በአጉማስ እኛ ኢትዮጵያውያን አብሮ የመብላት ብቻ ሳይሆን አብሮ የመስራት ባህላችንን እናዳብርበታለንም ሲል ይናገራል ወጣቱ አጉማሴ።

ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ምግብን በእጁ ይዞ ሳለ እንግዳ ቢመጣ እንብላ ማለት የለመደ ነው። ይህን ባይል ደግሞ “እንብላ አይባልም እንዴ?” ተብሎ በእንግዳው በነገር ሸንቆጥ ይደረጋል። እርሱም ይሉኝታ ይዞት “ይቅርታ ዘንግቼው እኮ ነው” ብሎ እንብላ የሚል ግብዣ ያቀርባል። ይህንን ደግሞ አጉማስ በእጅጉ የሚያረጋግጥና የሚያዳብር ነው። ምክንያቱም በእርሱ ድግስ ዘርቶ እንዳጨደ ከባለቤቱ ይልቅ አላፊ አግዳሚው ነው ጠግቦ ወደቤቱ የሚሄደው። ስለዚህም በአጉማስ ውስጥ የነገ ተስፋን ማለምለም አለ፤ አብሮነትን ማጎልበትም እንዲሁ አንዱ መገለጫው ነው።

ወጣቱ አጉማሴ ይህ ወቅት የሚታለፈው በዚህ አይነት ባህላችን ውስጥ ስንጓዝ ብቻ ነው ባይ ነው። ምክንያቱም ከመሰባሰብ ይልቅ መራራቅን የመረጥንባቸው ረጃጅም ጊዜያትን እንድናሳልፍ የሆነው በባህላችን መመራት ባለመቻላችን ነው።

የእኔ እንጂ የእኛን እየረሳን በመሆናችን ነው። አብሮነታችንን መገንባት ሳይሆን ማፈራረስን እየለመድነው ስለመጣን ነው። ስለሆነም አሁን በቃን ማለት አለብን። እነዚህን ባህሎቻችንን በመጠቀም ለለውጥ መነሳት ይኖርብናል። የሚበታትነንን አዲስ ባህል መቀበል ሳይሆን የሚያጠነክረንን ነባር ባህላዊ እውቀታችንን መጠቀም ይገባናልም ሲል ይመክራል። እኛም የራስ የሆነ ባህል ሀገር አልሚ ነው። ወደ አንድነታችን ይመልሰናል። ገንዘብን ብቻ ሳይሆን ወዳጅነትን ያጠብቅልናል። ስለዚህም አጉማስን የመሰሉ ባህላዊ ስርዓቶች ይጎልብቱ የሚለውን መልዕክት በማስተላለፍ ሃሳባችንን እንቋጫለን። ሰላም!!

ማህበራዊ

# ወጣቶች

# ትምህርትን ከተግባር አዳምሮ ሥራ የፈጠረው ወጣት

**ሰላማዊት ውቤ**



ወጣት ሶሽ ፋሪ

**«ዩኒቨርሲቲ ለእኛ ለወደፊት እድገትና የተቃና ስኬታማ ሕይወት መሰረት ነው የሚጥልልን። ሌላውን በራሳችን ጥረት እየሞከርን ነው ማግኘት ያለብን» የሚለው ወጣቱ የራሱን ተሞክሮም በማሳያነት ይጠቅሳል። ሆኖም በአንዳንድ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ዘንድ ያለው ምልከታ በተሳሳተ መልኩ መሆኑን ያስረዳል። ዩኒቨርሲቲ ፍፁም አድርጎ ያበቃኛል ወይም በተማርኩት ብቻ ገበያ ውስጥ ገብቼ እሰራለሁ የሚል እንደሆነ ይገልፃል**

ወጣት ሶሽ ፋሪ የቪንቴጅ ቴክኖሎጂስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር መሥራችና ሥራ አስኪያጅ ነው። ካንፓኒው የሶፍት ዌር ማበልፀግ ሥራ ላይ የተሰማራ ሲሆን ኩባንያውን መመስረትና ወደ ሥራ መግባት ብሎም፤ ለሌሎች ወጣቶች የሥራ ዕድል መፍጠር የቻለው ከዩኒቨርሲቲ ተመርቆ በወጣ በአንድ ወር ዕድሜ ውስጥ ብቻ ነው። ወጣቱ ከዚሁ ጎን ለጎን በሶፍትዌር ማበልፀግ ሙያው ለአገሩም የነፃ በጎ ፈቃድ ሥራዎችን በመስራትም ትልቅ አስተዋጾ አበርክቷል። እያበረከተም ይገኛል። ሶሽ ካበረከታቸው ሥራዎች መካከል በቅርቡ ተመርቆ ወደ ሥራ የገባው "ብሔራዊ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት አስተዳደር የመረጃ ቋት" ይጠቀሳል።

ወጣት ሶሽ ተወልዶ ያደገው በሻሸመኔ ከተማ ውስጥ ነው። ቤተሰቦቹ ነፃነት የሚሰጥ እና ልጆቻቸው ሀሳብ ሲያመጡና አንድ ነገር የማድረግ ፍላጎት ሲያድርባቸው የማይቃወሙ መሆናቸው አሁን ላለው ማንነቱ ትልቅ መሰረት የጣለለት መሆኑን ይናገራል። «በእነሱ አቅም መሞከር የሚችሉትን ሁሉ እንዲሞክሩ ይፈቅዳሉ። መሞከር የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥሩና ነፃነቱንም ይሰጣሉ» ይላል። በተለይ ቢሞክሩት አይጎዱም ብለው የሚያስቧቸው ላይ ሙሉ ፍቃድ ይሰጧቸው እንደነበር ይገልፃል። ወላጆቻቸው ትምህርት ላይና የቤተሰብ ጉዳይ ላይ ጥብቅ ቁጥጥር ቢያደርጉም ከዛ ውጭ ፍጹም ነፃነት የሚሰጡ መሆናቸው በራሱ እንዲተማመንና አዳዲስ ነገሮችን ለመሞከር ተስፋ እንዳይቆርጥ ያገዘው መሆኑን ያስረዳል።

«በተለይ የመንግስት ሠራተኛ የነበረው አባታችን በጣም አንባቢ ነበር» የሚለው ወጣቱ ሶሽ አባታቸዉ ገና የመጀመሪያ ደረጃ ተማሪ ሳሉ ጀምሮ ለነሱ ዕድሜ የሚመጥኑ መጽሐፍቶችን እንዲያነቡ ዕድሉን ያመቻቹላቸው እንደነበርም ያስታውሳል። ከዚሁ ጎን ለጎንም ኑሮን ለማሻሻል የሚያግዙ የገንዘብ አጠቃቀም ስልቶችን እንዲሁም ከሁሉም ጋር እየተጋገዙና እየተደጋገፉ በሰላም አብሮ መኖር የሚያስችሉ የእርስ በእርስ መስተጋብሮችንና እሴቶችን በአግባቡ እንዲገነዘቡም ያደርጓቸው ነበር።

ወጣቱ የቤተሰብ አስተዳደግ ስርዓቱን ጠቅለል አድርጎ ሲገልፀው «ቤተሰባችን እኛን በዚህ መልኩ በመቅረጽ በራስ መተማመን ያለው፤ ብዙ ነገር በነፃነት የሚሞክርና ፍርሃት የማያድርበት ዓይነት ሰው ለመፍጠር ሞክሯል ብዬ አስባለሁ» ይለዋል። ለዛሬ ማንነቱ የጠቀመውና አሁን ላለበት ደረጃ ያበቃው ይሄ ከታች ጀምሮ ሲገነባው የቆየው መልካም ስብዕና እና የአስተዳደግ ስርዓት ድምር እንደሆነም ደጋግሞ ይናገራል።

እንደወጣቱ ገለፃ፤ የቤተሰቦቹ መልካም አስተዳደግ ከአፀደ ህፃናት ጀምሮ እስከ 12ኛ ክፍል ያለውን ትምህርቱን በጥሩ ውጤት እንዲያጠናቅቅ አግዞታል። የ12ኛን የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተና ከወሰደ በኋላ ባመጣው ጥሩ ውጤት በማምጣቱ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኮምፒውተር ሳይንስ ትምህርት ክፍልን መቀላቀል ቻለ። የዩኒቨርሲቲው ቆይታው በልዩ ሁኔታ ያሳለፈው ይህ ወጣት በተለይ የአራተኛ ዓመት ተማሪ ሆኖ አንዳንድ ድርጅቶች ላይ በመስራት ገና ሳይመረቅ ብቃቱን አስመስክሯል።

ተቀጥሮ ለሚሰራባቸው ድርጅቶች ትንንሽ ሶፍትዌሮችን እየሰራ የሚያገኘውም ብር በአግባቡ ያስቀምጥ እንደነበር የሚናገረው ወጣት ሶሽ ልክ በ2008ዓ ዓ.ም በኮምፒውተር ሳይንስ ከዩኒቨርሲቲ ተመርቆ እንደወጣ ገንዘቡን የራሱን ድርጅት ለማቋቋም አጋጣሚውን የፈጠረለት መሆኑን ያስረዳል። ይህም ታዲያ ተመርቆ ከዩኒቨርስቲ ከወጣ በኋላ እንደ አብዛኞቹ ተመራቂ ወጣቶች በሥራ ፍለጋ አልተንከራተተም። የራሱን ኩባንያ መስርቶ ወደ ሥራ ለመግባትና ለሌሎች በእሱ ዕድሜ ላሉ ወጣቶች የሥራ ዕድል መፍጠር ከአንድ ወር በላይ ጊዜ አልፈጀበትም።

ቪንቴጅ ቴክኖሎጂስ ኃላፊነቱ የተወሰ የግል ማህበር የተሰኘው ኩባንያው ነሐሴ 2008 ዓ.ም ሙሉ ሕጋዊ ዕውቅና አግኝቶ ወደ ሥራ መግባቱን ያስታውሳል። ታዲያ በዚህ ወቅት አንዳንዶች እንደ ተመረቀ ፈጥኖ የራሱን ኩባንያ በማቋቋም ወደ ሥራ የገባው ቤተሰብ የገንዘብ ድጋፍ አድርጎለት ወይም የሆነ ሰው ገንዘብ ሰጥቶት እንደሆነ አድርገው ያስቡ ነበር። በርግጥ እንደተመረቀ ምንም ልምድ ሳይኖረው፤ ገበያውን ሳያውቅ የራሱን ድርጅት ወደማቋቋም መግባት በጣም ከባድ መሆኑን ያውቃል። ይሁንና ሶሽ እንደተመረቀ ወደ ሥራ እንዲገባ ያስቻለው እውነታ የአራተኛ ዓመት ተማሪ ሆኖ ከትምህርት ሰዓት ውጪ በነበረው ትርፍ ጊዜ ውጪ ላይ መሥራቱና የተማረውንና አራት ዓመታት በጥሩ ንባብና በተለያየ ጥረት ሲያዳብረው የቆየውን ዕውቀት ወደ ተግባር ለመለወጥ መቁረጡ እንደሆነ ያምናል።

ሶሽ እንደሚለው፤ አንድ ተማሪ ዩኒቨርሲቲ ሲገባ ብዙ ዕውቀቶችን ይገበያል ተብሎ ይታሰባል። መምህራኖቹ የሰጡትን ሁሉንም ነገር በሙሉ ልቅም አድርጎ ይይዛል። በድምሩ ዩኒቨርሲቲ ፍፁም ያበቃል ተብሎ ይገመታል። በአገሪቱ የትምህርት ፖሊሲ ወይም ነባራዊ ሁኔታ ብዙዎች ዩኒቨርሲቲ ላይ መምህራኖቻችን በሚሰጡን ትምህርት ብቻ ገበያ ውስጥ ገብቶ የሚሰራበት ዓይነት ዕውቀት አይገኝም።

«ዩኒቨርሲቲ ለእኛ ለወደፊት እድገትና የተቃና ስኬታማ ሕይወት መሰረት ነው የሚጥልልን። ሌላውን በራሳችን ጥረት እየሞከርን ነው ማግኘት ያለብን» የሚለው ወጣቱ የራሱን ተሞክሮም በማሳያነት ይጠቅሳል። ሆኖም በአንዳንድ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ዘንድ ያለው ምልከታ በተሳሳተ መልኩ መሆኑን ያስረዳል። ዩኒቨርሲቲ ፍፁም አድርጎ ያበቃኛል ወይም በተማርኩት ብቻ ገበያ ውስጥ ገብቼ እሰራለሁ የሚል እንደሆነ ይገልፃል። ነገር ግን ይሄ አይነቱ ምልከታ ትክክል አለመሆኑን ይናገራል። ከዚያ ይልቅም ገበያ ውስጥ ገብቶ ለመሥራት የሚያበቃው የራስ ጥረት እንደሆነ እና ተጨማሪ ዕውቀትና ንባብ አስፈላጊ መሆኑን ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት እንዳለባቸው ያመለክታል።

«ዩኒቨርሲቲዎች በተጨባጭ መሰረት ነው የሚሰጡን። መምህራኖቻችን ደግሞ መስመሩን ያሳዩናል። ከዚያ በኋላ ያለውን እኛ ነን በንባብና በተለያየ መንገድ የምናጎለብተው» ብሏል ወጣቱ ገበያ ውስጥ ገብቶ ለመሥራትና ተወዳዳሪ ለመሆን የሚያስችለውንና እሱ ስኬታማ የሆነበትን መንገድ ለዕድሜ አቻዎቹ ሲያመላክት።

የራሱን ኩባንያ ካቋቋመ በኋላ ሁለት ቦታ ይሰራ እንደነበር የሚገልፀው ወጣቱ የራሱ ኩባንያ ካማቋቋም ባለፈ በሌሎች ተቋማት ተቀጥሮ ይሰራ የነበረውም ልምድ ለማግኘትና በመስኩ ላይ ያለውን የገበያ ሁኔታ ለማወቅ እንደሆነም ይናገራል። «ምን ዓይነት ስትራቴጂዎችን እንደሚከተሉ ለማወቅ እንዲሁም በዘርፉ ልምዴን እንዳዳብር አግዞኛል» ሲልም ያስረዳል። ወጣቱ የራሱን ኩባንያ ሥራ ከማስኬድ ጎን ለጎን በቅጥር ይሰራ የነበረውን ሥራ አቁሞ ሙሉ በሙሉ ወደ ራሱ ድርጅት የተመለሰው በራሱ ለመቆም የሚያስችለው አቅም መገንባቱን ካረጋገጠ በኋላ እንደሆነም ነው የጠቆመው።

እንደወጣት ሶሽ ገለፃ፤ በራሱ የመቆም አቅም መገንባቱን ካረጋገጠ በኋላ በአጠቃላይ ኩባንያውን በመሰረተ በስድስት ዓመታት ውስጥ በርካታ ወጣቶችን መቅጠር ችሏል። ያሳተፈው ደግሞ በቋሚ እና በኮንትራት ቅጥር እንዲሁም የተማሪዎች የስራ ላይ ልምምድ ነው። በስራ ላይ ልምምድ ብቻ ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች የመጡ 40 ተማሪዎችን አስተናግዷል። ከነዚህ ውስጥም የራሳቸውን ሥራ እንዲፈጥሩና ተቀጥረው እንዲሰሩ ዕድል ያመቻችላቸው ተማሪዎችም ነበሩ።

«ከአዲስ አበባ፤ ከባህር ዳር፣ ከአዳማ፣ ከዲላ፣ ከድሬደዋ፣ ከአምቦ፣ ከጎንደር ዩኒቨርሲቲ የመጡ ተማሪዎች የራሳቸውን ሥራ እንዲፈጥሩና ተቀጥረው እንዲሰሩ ካደረግናቸው ውስጥ ይጠቀሳሉ» ይላል። በነዚህ ወጣቶች ስኬታማም ስራ መሰራት መቻሉን ጠቅሶ፤ በእሱ ፕሮግራም ውስጥ ከነበሩ ተለማማጅ ተማሪዎች ከፊሎቹ የራሳቸውን ስራ መጀመራቸውን፤ ቀሪዎቹ ደግሞ የተሻለ ደሞዝ ተከፋይ መሆናቸውንም ነው ያመለከተው። በተጨማሪም የውጭ አገር የትምህርት ዕድል ያገኙም፤ እየሞከሩ የሚገኙም እንዳሉ ተናግሯል።

በአሁኑ ወቅት አስር ቋሚ ወጣት ሠራተኞችና ሌሎችም የኮንትራት ሠራተኞች እንዳሉት የሚናገረው ወጣቱ በአገሩ ውስጥ ኩባንያ መስርቶ ገንዘብ ከማግኘት ጎን ለጎንም በርካታ ነፃ የበጎ ፈቃድ አገልግሎቶችን ከወጣቶች ጋር በመቀናጀት እየሰራ ስለመሆኑም ያስረዳል። ወጣቱ በዚህ በኩል ከአቻዎቹ ጋር እየሰራቸው ያሉት ነፃ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሥራዎች በርካታ ቢሆኑም በቅርቡ ተመርቆ ለአገልግሎት የበቃው "ብሄራዊ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት አስተዳደር የመረጃ ቋት" ሳይጠቀስ የሚያልፍ አይደለም።

ወጣቱ ይሄን የመረጃ ቋት መሥራት ያስቻለው አንድ ዕለት ማለዳ በቴሌቪዥን የተመለከተው ዜና እንደሆነ ይጠቅሳል። «ከውጭ አገር የመጣ የህክምና ባለሙያ በእረፍት ጊዜው በሙያው አገሩን በበጎ ፈቃደኝነት ለማገልገል ቢፈልግም የሚሄድበትን ቦታ ባለማወቅ መቸገሩን ሲናገር ሰማሁ» ሲል መነሻውን ያስታውሳል። ይሄንኑ በቴሌቪዥን ያየውን ቅሬታም መሰረት አድርጎ «አገራችን ላይ ነው፤ ገንዘብ እየሰራን ነው ያለነው። ሁሌ ከአገር ብቻ አይወሰድም፤ ለአገራችንም መስጠት አለብን» ሲልም የመረጃ ቋቱን በመሥራት በሙያው ለአገሩ ነፃ አስተዋጾ ማበርከቱን ይናገራል።

ሶሽ እንደሚለው እንደኛ አገር ተጨባጭ ሁኔታ ወጣቶች ብዙ ጥያቄዎችን ሲጠይቁ ይታያል። ብዙ የጎደሉንና ሊሟሉ የሚገቡ ነገሮች በመኖራቸው ጥያቄ መጠየቃቸው ትክክል ነው። ይሁንና ጥያቄውን ሲጠይቁ የአቅማቸውን አበርክተው ቢጠይቁ የተሻለ ነው። በተለይም ወጣቱ በተሰማራበት ሙያ ራሱን ማብቃት ይጠበቅበታል። በተሰማሩበት መስክ ተወዳዳሪ ሊያደርገኝ የሚችል ክህሎቱ አለኝ ወይ? ብለው ራሱን መጠየቅ አለባቸው።

ተመርቀው በሚወጡበት ዘርፍ «የስራ ዕድል ቢሰጠኝ መሰረታዊ የሆኑትን ስራዎችን እንኳን መስራት እችላለሁ ወይ?» ብሎ ራስን መጠየቅም እንደሚገባ ይጠቅሳል። «ከዩኒቨርሲቲ ዲግሪውን ይዤ በመውጣቴ ብቻ ብቁ ነኝ ማለት አይገባም። አስቀድሞ እኔ ተወዳዳሪ የሚያደርገኝ ብቃት ላይ ደርሻለሁ የሚለው ጥያቄ ውስጥ መግባት አለበት» ሲል አበክሮ ይናገራል።

አክሎም « ብዙ ወጣቶች ሰቅለው ደህና ውጤት በማምጣት መውጣትን ብቻ ነው የሚፈልጉት። ስለዚህም ድርጅቶች ሲቀጥሩ ብቃታቸውን እንጂ ሰቅለው የተመረቁትን ውጤት አይተው ቀጥሮ አያውቅም» በማለት ይገልፃል።

ወረቀቱ ሊጠቅማቸው የሚችልበት ቦታ ሊኖር በመቻሉ መስማማቱን የሚናገረው ሶሽ ገበያው የሚፈልገው የሚሰጣቸውን ሥራ የሚወጡበት አቅም ላይ የደረሱ ሰዎችን እንደሆነ ያሰምርበታል። በመሆኑም ወጣቶች ከዩኒቨርሲቲ ሲወጡ ዲግሪያቸውን የሚመጥን ብቃት ይዘው መውጣት አለባቸው» ሲልም መልክቱን አስተላልፏል።

# የምድር በረከት

# በጥናት የታገዘ ህገወጥነትን የመከላከል ድርሻ

**ስምስም መንግሥቱ**

የማዕድን ሀብት በባህሪው አላቂ ነው። ይሁን እንጂ በአግባቡ ጥቅም ላይ ከዋለ ለሌሎች ዘርፎች መልማት የማይተካ ሚና ያለውና በኢኮኖሚው እሴት የሚጨምር አዋጭ ኢንደስትሪ ስለመሆኑ መረጃዎች ያሳያሉ። ማዕድንን ማልማትና ማበልፀግ ለኢንደስትሪ፣ ለግንባታ፣ለግብርናና ለሌሎችም ግብአት በመሆን ከሚኖረው ድርሻ በተጨማሪ ለዜጎች የሥራ ዕድል በመፍጠርም የመንግሥትን ጫና በመቀነስ ከፍ ያለ ሚና አለው። በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ በግብርናው ዘርፍ የውጭ ምንዛሪን በማስገኘት የመሪነቱን ሚና የያዘው አረንጓዴው ወርቅ ተብሎ ከሚጠራው ቡና ቀጥሎ የማዕድን ዘርፍ የውጭ ምንዛሪ ምንጭ ስለመሆኑም መረጃዎች ይጠቀማሉ።

ከ2004 እስከ 2005 በነበሩት ዓመታት ከአጠቃላይ የወጪ ንግድ ገቢ ውስጥ በማዕድን ዘርፍ በተለይም ወርቅ 19 በመቶ ድርሻ እንደነበረው ይታወሳል። በተለይ ደግሞ በ2004 በጀት ዓመት 602 ነጥብ 4 ሚሊዮን ዶላር በማስገኘት ከቡና ቀጥሎ የውጭ ምንዛሪ ምንጭ ለመሆኑ የማዕድን ሚኒስቴር ነሐሴ 2012 ዓ.ም አዘጋጅቶ ከነበረው ረቂቅ የማዕድን ሀብት ልማት ፖሊሲ የተገኘው መረጃ ያመለክታል። በ2010 ዓ.ም ላይ በዓለም አቀፍ የወርቅ ዋጋ መውረድና በአገር ውስጥ በተፈጠረው አለመረጋጋት ለአገራዊ ምርትና ለወጪ ንግድ የነበረው አስተዋጽኦ ወደ ዜሮ ነጥብ አራት እና ሶስት ነጥብ ስድስት መቀነሱን ከሰነዱ የተገኘው መረጃ ያመለክታል። የማዕድን ዘርፉ ትኩረት እንደሚያስፈልገውም ሰነዱ ጠቁሟል።

የማዕድን ግብይት በዓለም ዋጋ ላይ መሠረት ያደረገ በመሆኑ በዋጋ መዋዠቅ ይፈተናል።ልማቱም ከሰላም ጋር ይያያዛል። በመሆኑም የልማት አካባቢ ከፀጥታ ስጋት ነጻ ካልሆነ፣በቴክኖሎጂ የታገዘ ልማት ለማከናወን ኢንቨስትመንቱ ከፍተኛ በመሆኑ የተለየ ትኩረትና ዋስትና ይጠይቃል። ለዚህም ነው ዘርፉ ልዩ ትኩረት ያስፈልገዋል የሚባለው። ማዕድን ከሌሎች ኢንደስትሪዎች ጋር እንዲተሳሰርና ለአገር ልማትም ተገቢውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ለማስቻል አስፈላጊው ሥራ መሰራት እንዳለበት የዘርፉ ባለሙያዎች ይመክራሉ።

መንግሥት በአገርበቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ውስጥ ማዕድንን አንዱ የልማት ዘርፍ በማድረግ በማዕድን ልማትና ግብይት ላይ የሚስተዋሉ ክፍተቶችና ተግዳሮቶች እንዲፈቱ በማድረግ ዘርፉ በአገር ምጣኔ ሀብት እድገት ላይ ጉልህ ሚና እንዲኖረው ለማስቻል የተለያዩ ጥረቶችን ሲያደርግ ቆይቷል።

ዘርፉ በመንግሥት ትኩረት አግኝቶ የዜጎችንም የአገርንም ተጠቃሚነት ማሳደግ እንዲችል የተለያዩ ሥራዎች ተሰርተዋል። ይሁንና የፀጥታና አለመረጋጋት፣ ህገወጥ ግብይት፣የጌጣጌጥ ማዕድናት ለገበያ የሚቀርብበት መነሻ ዋጋ አለመቀመጥ ከዘርፉ ሊላቀቁ ያልቻሉ ማነቆዎች ናቸው። በጌጣጌጥ ማዕድናት በዓለም ገበያ ተፈላጊና የውጭ ምንዛሪ በማስገኘት ትልቁን ድርሻ የያዘው ኦፓል ማዕድን ለህገወጥ ግብይት መዳረጉና የመሸጫ መነሻ ዋጋ ባለመውጣቱ የአገርን ጥቅም እያሳጣ ስለመሆኑ፣ ለኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ መግባት የነበረበት የወርቅ መጠን እያሽቆለቆለ መምጣት በዘርፉ በስፋት ይነሳል። ለእነዚህ ክፍተቶች መፍትሄ ለመስጠት መንግሥት እርምጃዎችን እየወሰደ ቢሆንም ዘላቂ መፍትሄ እያስገኘ አይደለም።

ችግሮች መፍትሄ እንዲያገኙ እርምጃ መውሰድ የመንግሥት ኃላፊነት ቢሆንም ችግሩን የጋራ አድርጎ የጋራ መፍትሄ በመፈለግ ረገድ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ይኖራሉ። ከባለ ድርሻዎች መካከልም ባለሙያዎችን በማፍራትና የምርምር ሥራ በመሥራት ላይ የሚገኙት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት (ዩኒቨርሲቲ) መምህራን ይጠቀሳሉ።እኛም ለዘርፉ ካላቸው ቅርበት አንጻር በማዕድን ዘርፉ ላይ የሚስተዋሉ ክፍተቶችን እንዴት እየታዘቡት እንደሆነና ችግሩንም የጋራ አድርጎ የመፍትሄ ሀሳብ ላይ ሊኖራቸው ስለሚችለው ድርሻ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲና በባህርዳር ዩኒቨርሲቱ የሥነምድር ሣይንስ (ጂኦሎጂ) ትምህርት ክፍል መምህራንን አነጋግረናል።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አራት ኪሎ በሚገኘው የሥነምድር ሣይንስ (ጂኦሎጂ) ትምህርት ክፍል መምህር ዶክተር ወራሽ ጌታነህ፤ የትምህርት ተቋማትን ጨምሮ ባለድርሻዎች በተለያየ መንገድ መንግሥትን ማገዝ የሚችሉበት ሁኔታ ቢኖርም በህግ የሚፈታውን በመፍታት ረገድ ስልጣንና ኃላፊነቱ የመንግሥት ነው ይላሉ። ከልማት እስከ ገበያ ያለው ሰንሰለት በህግ መመራት እንዳለበትና ህግ ሲጣስም በጠንካራ ህግ መመከት እንዳለበትና አሁን በዘርፉ ላይ እየታየ ላለው ህገወጥነት መስፋፋት ህግ ለማስከበር ካለው ጥንካሬ ጋር ያያይዙታል።መንግሥት ህግ የማስከበር አቅሙን ከፍ ማድረግ ካልቻለም ችግሩ በቀላሉ ይፈታል የሚል እምነት የላቸውም።

‹‹በድንበር በኩል የቁም እንስሳት በህገወጥ እንደሚወጡት ሁሉ የማዕድን ሀብቱም በተመሳሳይ ችግር እየገጠመው ነው›› የሚሉት ዶክተር ወራሽ፤ መንግሥት በሌላ ሥራ በተጠመደበት አጋጣሚ በማዕድን ዘርፉ ላይ የተፈጠረው ህገወጥነት ከአቅም በላይ የሚመስል ሁኔታ ቢኖርም ህግ የማስከበሩ ተግባር ልማቱ በሚከናወንበት እስከ ታች ቀበሌ ድረስ በተዘረጋ አሰራር መታገዝ ከቻለ መከላከል እንደሚቻል አመልክተዋል።

ዶክተር ወራሽ ሌላው ያነሱት ለህገወጥ ተግባር ገፊ የሆኑ ምክንያቶችን መፈተሽ እንደሚያስፈልግ ነው። እርሳቸው እንዳሉት የውጭ ምንዛሪ የማግኘት ጉዳይ በመሆኑ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ የሚረከብበት ዋጋና እና በኮንትሮባንድ ወይንም በህገወጥ የሚሸጥበት ዋጋ መካከል ያለውን ልዩነት ማየትና ውሳኔም መስጠት ይፈልጋል። አልሚው ለገበያ የሚያቀርብበት ወይንም የሚያስረክብበት ስፍራም ለህገወጥ ገበያ የተጋለጠ ነው።በልማቱ አቅራቢያ ግብይት የሚከናወንበት ባለመቻቸቱ አልሚው ማዕድኑን ወደ ገበያ ይዞ ሲሄድ በህገወጦች የመነጠቅና እነርሱ በሚፈልጉት ዋጋ እንዲያቀርብላቸው የመገደድ ሁኔታ ይፈጠራል። ህገወጦች አቅራቢያ ላይ ገበያ አለመኖርንና የህግ መላላትን ተጠቅመው የሚፈልጉትን እንዳያደርጉ ማድረግ አንዱ መፍትሄ እንደሆነም ሀሳብ ሰጥተዋል። እንዲህ ያለው የዘርፉ ተግዳሮት በሌሎችም አገሮች በተመሳሳይ እንደሚያጋጥም ተሞክሮዎች መኖራቸውንና የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ህገወጥነትን እንደሚከላከሉ ጠቁመዋል።

የመንግሥትን ኃላፊነትና ድርሻ እንዲሁም መፍትሄ ያሉትን እንዲህ ከገለጹልን በኋላ፤ በትምህርት ተቋማትና ከዘርፉ ባለድርሻ አካላት የሚጠበቀውንም እንደሚከተለው አስረድተዋል፤ ምንም እንኳን ህገወጥነቱ ከግንዛቤ እጥረት በመጣ እየተፈጸመ ነው የሚል እምነት ባይኖርም ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ካላቸው የማስተማር ተልእኮ አንጻር የጋራ ሥራ ለመሥራት የሚያስችል የምክክርና ግንዛቤ መፍጠሪያ መድረኮች በማመቻቸት ሚናቸውን ሊወጡ የሚችላባቸው እድሎች አሉ።

የህገወጥነትን ሰንሰለት የሚያሳይና መፍትሄም የሚሆን በጥናትና ምርምር የታገዘ መረጃ ለመንግሥት መስጠት የሚቻልበት እድል፣ ወይንም ችግሩን የጋራ እናድርገው የሚል መነሳሳት የለም ወይ? በሚል ለቀረበላቸው ጥያቄም ዶክተር ወራሽ ‹‹በእርግጥ መንግሥት ህገወጥነትን ሊከላከልባቸው የሚችላቸው ዘዴዎች ምን? ምን? ናቸው። የሚለው ላይ በመሥራት ማሳየት እንችላለን። ይገባልም። የህገወጥ ንግድ ሰንሰለት ላይ ጥናት በማድረግ የት ላይ ቢሰራ ውጤታማ የሆነ የሀብት ቁጥጥር ማድረግ እንደሚቻል ማመላከት ይቻላል›› በማለት ምላሽ ሰጥተዋል።

በአንድ ወቅት ከተማሪያቸው ጋር በአማራ ክልል ወሎ ደላንታ አካባቢ በኦፓል ማዕድን ልማት ላይ ከአልሚዎቹ ጀምሮ ለገበያ እስኪቀርብ ባለው ሂደት፣ ልማቱ በአካባቢ ላይ ሊያሳድር ስለሚችለው ተጽዕኖ፣ የአካባቢ ማህበረሰብንም ተጠቃሚ በማድረግ ረገድ እየተከናወኑ ስላሉ ተግባራት ላይ ባደረጉት መለስተኛ ጥናት የህገወጥነት ድርጊት በተለያየ ሰንሰለት ውስጥ አልፎ እንደሚፈጸም መለየት ችለዋል። በጥልቀት ለማወቅ የሚያስችል መረጃ ለማግኘት ቀላል ሆኖ ባያገኙትም አልሚው፣ ማዕድን አውጪው ወይንም ቆፋሪው፣አልሚዎችን ቀጥሮ የሚያሰራ፣ ማዕድኑን ተቀብሎ ለአገር ውስጥና ለውጭ ገበያ የሚያቀርበው፣ ደላላ እነዚህ ሁሉ ተዋናይ መሆናቸውን በመለስተኛ ጥናታቸው መፈተሽ ችለዋል። አንዳንዴ አልሚዎች ያለሙት ማዕድን ወዴት እንደሚሄድ ተቀባያቸውም ማን እንደሆነ መረጃ የማያገኙበት አጋጣሚ መኖሩንና ይህም ህገወጥነቱ ምን ያህል በጥንቃቄ እንደሚከናወን የሚያሳይ እንደሆነ ጥናቱ አሳይቷል።

የሰንሰለቱ መርዘም ችግሩን ውስብስብ እንደሚያደርገው፣ መካከል ላይ ባለው ሰንሰለት መርዘም ህገወጥ ድርጊቱን የሚፈጽመውን ዋና ተዋናይ ለማግኘት አስቸጋሪ እንደሆነ መረዳት እንደሚቻል የጠቆሙት ዶክተር ወራሽ፤ ሰንሰለቱን በዚህ መንገድ ለይቶ የት ላይ ሰንሰለቱን መስበር ወይንም መበጠስ ይቻላል የሚለው ሰፊ የጥናት ሥራ እንደሚጠይቅ አመልክተዋል።በቀጥታ ከአልሚዎች ጋር ግንኙነት መፍጠርና እነርሱን የሚያነቃቃ ሥራ መሥራትም ሌላው የህገወጥ ድርጊትን መከላከያ መንገድ ሊሆን እንደሚችልና በህገወጥ ድርጊት ላይ የተሰማሩትንም ቢሆን ወደ መንግሥት የሚሳቡበትን ሁኔታ መፍጠርም ችግሩን ለመቀነስ ይረዳል ብለዋል። እንዲህ ያሉ ሀሳቦችን በማመላከት የትምህርት ተቋማት ሚና ሊኖራቸው እንደሚችል ገልጸዋል።

ዘርፉ ላይ የሚስተዋለው ክፍተትና ማነቆ ወደፊት በዘርፉ ለመሰማራት በትምህርት ገበታ ላይ ለሚገኙት ተስፋ የሚያስቆርጥ ሊሆን ይችል እንደሆን በስጋት ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ፤ ተስፋ የሚያስቆርጥ ነገር የለም። እንደውም ብዙ ተስፋ ነው ያለው። ለዜጎች የሥራ ዕድል የሚፈጥር የማዕድን ሀብት ኢትዮጵያ ውስጥ ይገኛል። በአገሪቱ ውስጥ የተፈጠረው አለመረጋጋት ችግር ህገወጥነቱን ያባባሰው በመሆኑ እንጂ ሰላም ሲፈጠር የሚስተካከል እንደሆነ አስረድተዋል።

ማዕድንን ማንኛውም ሰው በቦርሳውና በኪሱ ይዞ መዘዋወር መቻሉ ለህገወጥ ተጋላጭነቱን እንደሚጨምር የጠቆሙት ዶክተር ወራሽ፤ ይህ በመሆኑም ማዕድን ከሌሎች ዘርፎች በተለየ የሀብት አስተዳደር እንደሚያስፈልገውና መንግሥትም ይህን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ሀብቱን ሊያስተዳድረው ይገባል ብለዋል።

በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ የሥነምድር ሳይንስ (ጂኦሎጂ) ትምህርት ክፍል ዲን ዶክተር ምንያህል ተፈሪ በበኩላቸው በማዕድን ዘርፍ ለሚስተዋለው የህገወጥነት መስፋፋት የህግ መላላት እንደሆነ ነው የገለጹት። መንግሥትን ጨምሮ ባለድርሻ አካላት የየራሳቸው ተልእኮና ተግባር እንዳላቸውና በተሰጣቸው ኃላፊነትም የየድርሻቸውን እንደሚወጡም አመልክተዋል። በዚሁ መሠረት ህግን ማስከበርና ህገወጦችንም በህግ መከላከል የመንግሥት ድርሻ እንደሆነና ጠንከር ያለ ህግ በማውጣት ለችግሩ መፍትሄ መስጠት ይጠበቅበታል ብለዋል።

የትምህርትተቋማትዋናተልእኮሀብቱየሚገኝባቸውን አካባቢዎች፣ የሀብት መጠኑንና ጥራቱን በጥናት ለይቶና በሰነድ አዘጋጅቶ ልማቱን ለሚያስተዳድረው አካል መስጠት እንደሆነ በመጠቆም፤ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲም ‹‹የማዕድን ልማት ስትራተጂክ ዶክመንት›› ወይንም ፍኖተካርታ አዘጋጅቶ ለክልሉ ማዕድን ሀብት ልማት ቢሮ መስጠቱን ገልጸዋል።በዚህ ሰነድ ውስጥም ህገወጥነትን ለመከላከል መሰራት ሥላለበት ሥራ ለማመላከት ጥረት መደረጉን ገልጸዋል።ማዕድን ላይ የሚፈፀመው ህገወጥነት በሌላ ጉዳይ በሚፈጸም የወንጀል ድርጊት ላይ ህጋዊ እርምጃ እንደሚወሰድ ሁሉ ማዕድንን ለግል ጥቅማቸው በማዋል የአገርን ጥቅም በሚያሳጡት ላይ ጠበቅ ባለ የህግ ማእቀፍ እርምጃ መውሰድ ይገባል ብለዋል።

ዩኒቨርሲቲዎች ካላቸው ተልእኮዎች አንዱ የማሕበረሰብ አገልግሎት መስጠት እንደሆነ ይታወቃልና ከዚህ አንጻር ልማቱ በሚከናወንበት ስፍራ ላይ ሊሰራ የሚችል ስራ ይኖር እንደሆነም ዶክተር ምንያህል ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ፤ ዩነቨርሲቲው በዚህ ረገድ ከሚሰራቸው ሰፊ ሥራዎች መካከል አንዱ የማዕድን ልማት በሚከናወንበት አካባቢ ነው።ማዕድኑ በህገወጥ ከአገር እንዲወጣ ከመደረጉ በተጨማሪ እሴት ሳይጨመርበት ለውጭ ገበያ መቅረቡ በራሱ የተሻለ የውጭ ምንዛሪ እንዳይገኝ ያደርጋል። በመሆኑም እነዚህን መሠረት በማድረግ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት እንደሚሰጥ ገልጸዋል።

**‹‹በእርግጥ መንግሥት ህገወጥነትን ሲከላከልባቸው የሚችሉባቸው ዘዴዎች ምን? ምን? ናቸው፡፡ የሚለው ላይ በመሥራት ማሳየት እንችላለን። ይገባልም፡፡ የህገወጥ ንግድ ሰንሰለት ላይ ጥናት በማድረግ የት ላይ ቢሰራ ውጤታማ የሆነ የሀብት ቁጥጥር ማድረግ እንደሚቻል ማመላከት ይቻላል››**

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## የህይወት ቀለም

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ነገ ልደቱ ነው..ልደቱ ሲቀርብ ደስ አይለውም። በልደቱ ፊትና ኋላ ውስጥ ሰላም የለውም..ሀዘንተኛ ነው። የህይወቱ ውብ ቀለም መደብዘዝ የሚጀምረው በዚህ ሰሞን ነው። በህይወቱ ምርጥ የሚለውን ነገር በልደቱ ማግስት ያጣ ነው። አሁንም የሆነ ነገር የሚሆን ይመስለዋል። የሆነ ነገሩን የሚያጣ ይመስለዋል። ምኑን እንደሚያጣ ግን እርግጠኛ አይደለም ምክንያቱም ምንም የለውምና። በዚህ ሰሞን.. በዚህ ስሜት ከቤት መውጣት አይፈልግም ግን አንድ የማይቀርበት ቀጠሮ አለው። የልጅነት ጓዳኛው ከውጪ አገር መጥቶ እሱን ለማግኘት እየሄደ ነው። ልደት ባይኖረው.. እናቱ የተወለደበትን ቀን ባትነግረው ምንኛ ደስተኛ ነበር። ልደቱ ደርሶ በሰላም ወጥቶ የገባበት ቀን የለም። ገደቢስነቱ ከልጅነቱ የጀመረ ነው። ከሶስት ጓደኞቹ ጋር ወንዝ ወርደው ሲዋኙ ደራሽ ውሀ መጥቶ ሁለቱን ጓደኞቹን የነጠቀው በልደቱ ቀን ነበር። በልጅነቱ ስም ጠሪያቸውን ፈንክቶ ለአንድ ዓመት ከትምህርት የታገደው በዚሁ ቀን ነበር። እድለቢስነቱ ዩኒቨርሲቲ ገብቶም አልተወውም የመጀመሪያ ዓመት ተማሪ እያለ በጣም የሚወደውን ጓደኛውን በመኪና አደጋ ያጣው ለልደቱ የሚሆን እቃዎችን በመገዛዛት ላይ እያሉ ነበር። በዓመቱ ህያብን አጣት። ህያብ የህይወቱ የብዙ ነገር መጀመሪያ ናት። ዓለም እሷን ተደግፋ የቆመች ይመስለዋል። በፍቅሯ፣ በውበቷ የቆነጀች ይመስለዋል። የልክ ነገር መጀመሪያና መጨረሻ ይላታል። ይገርመዋል ዛሬም ድረስ በእሷ እውነት ነው የሚኖረው። በህይወቱ ውስጥ የእሷ አለመኖር ሁሌም ይቆጨዋል። በታሪኩ ውስጥ ደምቃ የደበዘዘች አንድ እውነቱ ናት። እንዴት እንደተለያዩ ሲያስብ እሷን ለመጥላት አንድ ምክንያት ያገኘ ይመስለዋል.. ግን ጠልቷት አያውቅም። በህይወቱ ውስጥ እንዲሆን የሚፈልገው አንድ ተዐምር ቢኖር የእሷ በእሱ ህይወት ውስጥ ዳግም መብቀል ነው። ግን መቼም የማይሆን ምኞት ይለዋል...

‹እንዴት ነበር የተለየችው? መቼም አይረሳውም..። በልደቱ ቀን ላይ ልደቱን እያከበሩ ነበር። ድንገት ስልኩ አንድ የፅሁፍ መልክት መቀበሉን ጮሆ ተናገረ። ስልኩ ህያብ ጋር ስለነበር..የተላከውን መልዕክት ከፍቶ ለማየት እድል ነበራት። መልዕክቱን አየችው..‹የኔ ፍቅር እንኳን ተወለድክልኝ። በጣም ነው የማፈቅርህ ያንተው ሳምራ› ይላል። ከዛ ቴክስት በኋላ ህያብ ዳግም ወደ ህይወቱ አልመጣችም። ስልኩን ብላክ ሊስት ውስጥ እስከጨመረችበት ጊዜ ድረስ እየደወለ ሊያስረዳት ሞክሮ ነበር ግን ስልክ ከመዝጋት ባለፈ የፈየደው አልነበረም። ጭራሽ እሱን ላለማየት ብላ ዩኒቨርሲቲ መቀየሯን ሰማ። በዚህ ሁሉ እውነት ልደቱን ይፈራዋል። በተለይ ሰዎች የሚሞቱበት ቀን ከተወለዱበት ቀን ጋር የተያያዘ ነው የሚል ጽሁፍ ካነበበ በኋላ ስጋቱ በእጥፍ ጨምሯል። ልደቱ በቀረበ ቁጥር ለሞት የቀረበ ይመስለዋል። እያጣቸው ያሉት ውድ ነገሮች የሞቱ ዋዜማ ይመስሉታል። ጭራሽ የልደቱን መምጣት ተከትሎ ሰሞኑን እንቅልፍ የሚባል በአይኑ አልዞረም። በተኛበት የሚሞት እየመሰለው ቁጭ ብሎ ማደርን ልማድ አድርጎታል። በዚህ ጊዜ ከቤት መውጣት አይወድም። ስራ በመቅረትም እንደልደቱ ሰሞን ሪከርድ የለውም። በቃ የሆነ መኪና ድንገት መጥቶ የሚገጨው ይመስለዋል። የሆነ ህንጻ ተደርምሶ የሚያጠፋው ይመስለዋል። በእግረኛ መንገድ ላይ እየሄደ እንኳን ሞቱን ነው የሚያስበው። አሁን ራሱ ለመሞት የሚሄድ ነው የሚመስለው። ጓደኛው ሞት ሆኖ የሚጠብቀው ነው የሚመስለው። ምን ነበር የልደት ቀኑን ባያውቀው..ምን ነበር ጳጉሜ 2ትን ባያውቃት። ብዙዎች የልደታቸውን መቅረብ ተከትሎ የእንኳን ደስ ያለህ መልዕክት ሲለዋወጡ፣ ሲደሰቱ፣ ሲጨፍሩ ሲያይ ይገርመዋል። ብዙዎች ልደታቸውን ለማክበር ቦታ ሲመርጡ፣ እንግዳ ሲጠሩ ሲያይ ያስቀናዋል። ብዙዎች የወዳጆቻቸውን ልደት በሰርፕራይዝ ሲያደምቁ፣ በኬክና በስጦታ ሲያስቡ ሲያይ በራሱ እንዲህ መሆን ይቆጫል።

በህይወቱ ሁለት ነገሮችን አብዝቶ ይፈራል አንዱ የልደት ቀኑ ነው..አንዱ ደግሞ የሞቱ ቀን። መኖር የሚወድ ሰው ነው። ህይወትን እስከ መጨረሻው የእድሜ ጥግ ድረስ መኖር ይሻል። ህይወት ብርቱ ናት..መኖር የምንጊዜም ህልሙ ነው። በህይወቱ ሁለት ሴቶችን አይረሳም..አንዷ መስህብ ናት አንዷ ደግሞ ህያብ። መስህብ ከህያብ እንዲለያይ በልደቱ ቀን ላይ የውሸት ቴክስት ጽፋ የላከችለት የዲፓርትመንታቸው የመጨረሻ ዓመት ተማሪ ናት። እንደምትወደው ብዙ ጊዜ ነግራው የሚወዳት ፍቅረኛ እንዳለችው ነግሯት ነበር። ህያብ የብዙ ነገር መጀመሪያው ናት..ምድርን ወደ ገነት የቀየረችለት፣ ህይወትን እንዲወድ እንዲያፈቅር ያደረገችው የነፍሱ ውብ ቅኔ። በመስህብ የውሸት ቴክስት አቅም አጥታ የራቀችው፣ እንደዛ ሲለምናትና ሊያስረዳት ሲሞክር የገፋችው..። እንደ አባትና እናቱ እኚህ ሁለት ሴቶች ህይወቱን ሙሉ ያመራምሩታል። መስህብ ፍቅርን አታውቅም። ፍቅር ለሚወዱት መኖር እንደሆነ ገና አልደረሰችበትም። ራሷን በማፍቀር የምትኖር ጭራቅ ናት። ህያብ ብዙ ፍቅር አላት..ፍቅሯ ግን እውነት የለውም። ከምታየው ይልቅ በምትሰማው ውስጥ ናት። እምነቷ መጨረሻ የለውም። በአእምሮዋ ሳይሆን በአካሏ ውስጥ የበቀለች እንዲህም ናት። ህያብ እውነት ቢኖራት ኖሮ ዛሬ ላይ አብረው ነበሩ..ደስ በሚል እንግዳ ዓለም ውስጥ።

ለእሱ ሁሌም ትክክል እናቱ ናት። የእናቱ ሀቅ አመራምሮት አያውቅም። በህይወቱ ውስጥ መቼም የማይረሳቸውን ሁለት እውነቶች አስቀምጣለች። አንዱ የፍቅር እውነት ነው..ከመስህብና ከህያብ የራቀ የፍቅር እውነት። ፍቅር ሞት የሌለበት ዓለም ነው። የሌሎች ጥላቻ የአንተን ህያው ፍቅር እንዳይገልብህ ሁሌም ከላይ ሁን› ስትል አደራ ብላዋለች። በዚህ እውነት ውስጥ የኖረው ለአጭር ጊዜ ብቻ ነው። ከእናቱ ህልፈት በኋላ በህይወት ያለ አባቱ የእናቱን የልጅነት እውነት የሚሽር ሌላ እውነት አስተማሩት ‹ፍቅር ሁሌም እውነት አይደለም። ፍቅር ሁሌም ጸዐዳ አይደለም። ፍቅር እውነት ቢሆን ኖሮ የመጀመሪያ ፍቅረኛዬን ትቼ እናትህን አላገባም ነበር። ፍቅር ውስጥ እውነት ብቻ ዋጋ የለውም። ዋጋህ ያለው በእውነትና በማስመሰል መካከል ነው ብለውታል። አሁን ላይ በየትኛው እውነት እንደሚኖር አያውቀውም። እናቱ ትሁን አባቱ ልክ ይሄንንም አያውቀውም። በህይወቱ ብዙ ቦታ ላይ እናቱን ልክ ሆና አግኝቷታል። በህይወቱ እጅግ ብዙ ቦታ ላይ የአባቱ እውነት ሲከተለው ደርሶበታል። ህያብ የማን እውነት ናት? የእናቱ ናት? የአባቱ? አያውቀውም። በሁለቱም እውነት ውስጥ ያለች ሌላ እውነት ትመስለዋለች። እሱን ማፍቀሯ..በነፍሷ ውስጥ ነፍሱን ማስቀመጧ የእናቱ እውነት ይመስለዋል። በውሸትና በማስመሰል ትልቅ ፍቅሩን መሻሯ..ትልቅ እውነቱን መግፋቷ፣ ሊያስረዳት ሲሞክር አለማድመጧ ደግሞ የአባቱ እውነት ይመስለዋል። በየቱ ይኑር? ዓለም የማን ናት? እውነቷ ምንድነው? ብዙ ጥያቄዎች አንድ ላይ ግር ብለው በልደቱ ዋዜማ ወደተጨናነቀው አእምሮው ገቡ። በዚህ ጊዜ ከቀጠሮው ቦታ ደርሶ ነበር።

በእናቱና በአባቱ እውነት እየዋለለ፣ ሞቱን እያሰበ ወደ አንድ ህንጻ ሊገባ ሲንደረደር..አንድ መኪና ክላክስ አደረገለት።

ለእሱ ስላልመሰለው ወደ ኋላ አልዞረም..።

ከመኪና ጡሩንባ ጋር የተቀላቀለ ‹ፍትህ..የሚል አንድ ቀጭን የሴት ድምጽ ጆሮ ግንዱ ላይ አንባረቀ።

ቆመ..። በቆመበት ይሄ ነው የማይለው በመኖርና ባለመኖር መካከል ያለ ስሜት ዋጠው። እንዲህ የሚጠሩት ሁለት ሴቶችን ያውቃል። አንዱ እናቱ ናት..አንዷ ደግሞ ህያብ። ሁለቱም አጠገቡ የሉም..ታዲያ ማን ሊሆን ይችላል? የልደቱ ማግስት አይደል..እየሞተ መሰለው እና ደግሞ ለዘላለም ህያው እየኖረ። የቱን ይመን? በእናቱና በአባቱ እውነት መካከል ቆሞ ወደ ኋላው ዞረ።

በተከፈተ መስኮት ያጮለቀ ቀይ እግዚአብሄራዊ ፊት ዓለም ላይ ምርጡን ፈገግታ ይዞ ይታየዋል..

‹እየሞትኩ ይሆን? ራሱን ጠየቀ። አብዛኞቹ መከራዎቹ ከዚህ ቀጥለው የመጡ ናቸው። አብዛኞቹ ስቃዮቹ ሳቁን ተከትለው የተከሰቱ ናቸው።

ወደ ፊቱ ሁለት ርምጃ ተራመደ። አይኖቹ በመስኮቱ አልፈው ቀይዋ ሴት ላይ ይንቀዋለላሉ። መላዐካዊ መልክ ወደ እሱ ፈገግ ብሎ ይታየዋል።

‹ይሄስ ምንድነው? የእናቱ ነው የአባቱ እውነት? ወይስ ያልደረሰበት ሌላ ሰማያዊ እውነት? ሳያስበው ሳቀ..የምንም ነገር መጀመሪያ በሆነ ቀን ላይ የቆመ መሰለው። እግሮቹ ተራምደው ከፈገግተኛዋ ሴት አጠገብ አደረሱት። ወደ እናቱ እውነት እየቀረበ ይመስለዋል። ዓለም በእናት እውነት ውስጥ ያለች መሰለው። በአባቱ እውነት ያጣውን ፍቅር በእናቱ እውነት አገኘው። እናት እውነት..አባት እምነት።

ቀይዋ ሴት ህያብ ነበረች።

እንደዛን ቀን መጥፎ ፊት አይቶ አያውቅም። ሴት ልጅ መሆንም እንደምትችል ያኔ ነው ያወቀው። ያጣት በዚሁ ቀን ነበር። ህያብ የህይወቱ ምርጥ ዩኒቨርሲቲ ተማሪ እያለ አሁንም ወደ ሞት እየሄደ ይመስለዋል።

# ዓለም አቀፍ

## ዓረብ ኢምሬትስ በሰብዓዊ መብት አያያዝ አድናቆትን ተቸረች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የተባበሩት ዓረብ ኢሚሬትስ የሰብአዊ መብት አጠባበቅ በሰብአዊ መብት መስክ በተሰማሩ ዓለም አቀፍ ባለሙያዎች ተወድሷል፡፡

በዓረብ ኢሚሬትስ የሰብአዊ መብት አያያዝ ላይ ያተኮረ ምክክር ትናንት ከጄኔቫ በበይነ መረብ ውይይት የተካሄደ ሲሆን አገሪቱ በጾታ እኩልነት፣ የኃይማኖት ልዩነትን በማክበርና በሰብአዊ መብት አያያዝ ረገድ ዓለም አቀፍ ሞዴል ልትሆን የምትችል መሆኗን የሰብአዊ መብት ተሟጋች ባለሙያዎች ተናግረዋል።

ዓረብ ኤምሬትስ በተለያዩ አገራት ሰው ሰራሽም ሆነ ተፈጥሮአዊ አደጋዎች በሚያጋጥሙበት ወቅት የምትሰጠው አፋጣኝ የሰብአዊ አገልግሎትም የሚደነቅ መሆኑን በሲምፖዚየሙ የተነሳ ሲሆን አገሪቱ መሰረታዊ መብቶችን ማለትም እንደ የግለሰብ ነጻነት፣ በጾታ መካከል እኩልነት እና እኩል እድልን በማረጋገጥ፣ የህጻናት፣ የአረጋውያን እንዲሁም የሰራተኛ መብቶችን በመጠበቅ ረገድ ያስመዘገበቻቸው አስደናቂ ውጤቶችም ተዘርዝረዋል።

አገሪቱ ህገወጥ የሰዎችና የገንዘብ ዝውውርና ሽብርተኝነትን በመዋጋት ረገድ የምትጫወተው ሚና በአርአያነት ሊጠቀስ የሚችል መሆኑንም ነው ባለሙያዎቹ ያነሱት፡፡



የዓረብ - አውሮፓ የውይይት እና የሰብአዊ መብቶች ፎረም ሊቀመንበር አይማን ናስሪ፣ የተባበሩት ዓረብ ኢሚሬትስ በሰብአዊ መብት አያያዝ ከዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ዘንድ ሰፊ አድናቆትን ማግኘቱን ተናግረው፤ አገሪቱ ለሶስት ጊዜያት የሰብአዊ መብቶች ምክር ቤት አባል እንደመሆኗ በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ቁልፍ አጋር ሆናለች ሲሉም አክለዋል፡፡

የዓለም አቀፉ የዲፕሎማሲ እና የውይይት ምክር ቤት ተባባሪ ዳይሬክተር ዶክተር ኤሪክ ጎዝላን በበኩላቸው፣ የተባበሩት አረብ ኤምሬትስ አመራር "የአብርሃም የሰላም ስምምነት" ለመፈረም የወሰደውን እርምጃን በማወደስ፤ ከእስራኤል መንግስት ጋር የተደረሰው ስምምነት በቀጣናው ዘላቂ ልማትን እና ብልጽግናን የሚያመጣ መሆኑንም አመልክተዋል፡፡

የተባበሩት ዓረብ ኢምሬት በሰብዓዊ መብት ጥበቃ ዘርፎች እመርታ ማስመዝገቧን በጄኔቫው የበይነ መረብ ውይይት ያስታወቀች ሲሆን ለዚህ ውጤት መብቃቷ በዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ጥበቃ መርሆዎች ላይ ያላት ተሳትፎ ንቁ መሆኑን በምክንያትነት ጠቅሳለች፡፡

አገሪቱ የሰብዓዊ መብት ሪፖርቷን የፊታችን ግንቦት ወር ላይ ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰብዓዊ መብት ምክር ቤት የምታቀርብ ሲሆን በሪፖርቱ ላይ ከ13 በላይ የዓረብ፣ የአውሮፓ እና ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች እና 17 ባለሙያዎች ተሳታፊ መሆናቸውንም ነው የገለጸችው፡፡

ዓረብ ኢምሬትስ በአገሯ ከ200 በላይ አገራት የተሰባሰቡ የዓለማችን ዜጎች የሚኖሩባት አገር ስትሆን ዜጎች መብቶቻቸው ተረጋግጦላቸው እንዲኖሩ በማድረግ ረገድ ያስመዘገበችው ውጤት አገራት በተምሳሌትነት ሊወስዱት ይገባል ተብሏል።



## የናይጄሪያ ሴኔት እጩ ተወዳዳሪ በጥይት ተገድለው አስከሬናቸው ተቃጠለ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የናይጀሪያ ሴኔት እጩ ተወዳዳሪ አይቦ ቹክው በጥይት ከተገደሉ በኋላ አስከሬናቸው መቃጠሉ ቢቢሲ አስነብቧል።

ፖለቲከኛው በደቡባዊቷ ኢኑጉ ግዛት ከምርጫ ቅስቀሳ ሲወጡም ጥቃት እንደደረሰባቸውና እንደተገደሉም የተገለጸ ሲሆን የሌበር ፓርቲ አባል መሆናቸውና ናይጄሪያ በመጪው ቅዳሜ በምታደርገው ብሔራዊ ምርጫም እጩ ተወዳዳሪ እንደነበሩም ተነግሯል።

ይህም ምርጫ በአገሪቱ በ24 ዓመታት ውስጥ ታይቶ የማይታወቅ ፉክክር የታየበት ምርጫ ተደርጎ እየተገለጸ ሲሆን አብረዋቸው የነበሩ የፖለቲከኛው ረዳቶቹም በጥይት ከተገደሉ በኋላም አስከሬናቸው በመኪናቸው ውስጥ አብሮ መቃጠሉን የአካባቢው ሚዲያዎች ዘግበዋል።

"የፓርቲያችን አባላት በክልሉ የሌበር ፓርቲ ዕውቅና ስጋት የጫረባቸው እና በቅዳሜው ምርጫ ልንሸነፍ ይችላል ብለው በሚሰጉ የፖለቲካ ፓርቲዎች የግድያ ኢላማ ተደርገዋል" ሲሉ የሌበር ፓርቲን ወክለው በግዛቲቱ አስተዳዳሪነት ለመወዳደር እጩ የሆኑት ቺጂዮኬ ኢዶጋ ገልጸዋል።

ሌበር ፓርቲ በጥቃቱ ላይ ይፋዊ መግለጫ ከመስጠት ቢቆጠብም በመጪው ምርጫ ናይጄሪያን ለመምራት እጩ ፕሬዚዳንት ሆነው የሚወደዳሩት የፒተር አቢ ደጋፊዎቻቸው “በትክክል፣ ሰላማዊ እና በተስፋ ተሞልተው” እንዲመርጡ ሲያሳስቡ ቆይተዋል።

# ባለሀብቶች በአነስተኛ ኤርፖርቶችና...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

ያቀርባል ብለዋል፡፡

የአየር ትራንስፖርት ሁለንተናዊ እድገት ለማረጋገጥ የኤርፖርቶች መሰረተ ልማት ማስፋፋት ቁልፍና ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው ያሉት አቶ ጌታቸው፤በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ አራት ዓለም አቀፍ የኤርፖርት ደረጃ የተሰጣቸውን ጨምሮ 22 መደበኛ አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ ኤርፖርቶች ቢኖሩም በቁጥርም ይሁን በሚሰጡት የአገልግሎት አድማስና ቅልጥፍና አኳያ ሲታዩ በቂና ተመጣጣኝ አይደሉም ነው ያሉት። ያሉትም በጣት የሚቆጠሩ አነስተኛ አውሮፕላን ማረፊያዎችም (Airstrips) ለሜጋ ፕሮጀክቶች፣ ማዕድን ለማውጣት፣ ለግብርና፣ ለመዝናኛ፣ ለሰብዓዊ እና ለተለያዩ አገልግሎቶች እየዋሉ እንደሚገኙ ገልጸዋል።

የአውሮፕላን ማረፊያዎች ማስፋፋት የአየር ትራንስፖርት አገልግሎትን ተደራሽነት ለማሳደግ ቀዳሚ ተግባር መሆኑን አመልክተው፤ይህም መንገደኞችና ዕቃን በፍጥነት ለማጓጓዝ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸውን እና በቀላሉ የሚበላሹ ምርቶችን በአስተማማኝና በጥራት ለማመላለስ፣ የቱሪዝም መዳረሻ ስፍራዎችን ተደራሽ በማድረግ ምርታማነትን ለማሳደግ ወሳኝ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

አቶ ጌታቸው ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት መስከ ከአፍሪካ ግንባር ቀደም ብትሆንም ካላት የህዝብ ብዛትና ሰፊ የቆዳ ስፋት አኳያ ለሀገር ውስጥ የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት በሚውሉ የአነስተኛ ኤርፖርቶች ልማት በኩል ከሌሎች ሀገራት ጋር ሲነፃፀር እጅግ በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች። ከምክንያቶቹ አንዱ የኤርፖርቶች ግንባታና አስተዳደር በዋናነት በፌዴራል መንግስት ጫንቃ ላይ የወደቀ መሆኑ ነው ብለዋል።

እናም አነስተኛ ኤርፖርቶች እና ሄሊፖርቶች ግንባታ እና አስተዳደር ላይ የግል ባለሀብቶችን፣ የክልል መንግስታትን፣ የከተማ መስተዳድሮችን እና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትን በስፋት ማሳተፍ አስፈላጊ ነው። ከዚህ በፊት በአቬዬሽን ዘርፍ የተሰማሩ ባለሀብቶችን የሚያጋጥማቸውን ችግር ለመፍታትና ለማበረታታት እየተሰራ ስለመሆኑም ተናግረዋል፡፡

የግሉ ዘርፍና የክልል መንግስታት በአቬዬሽን ዘርፉ እንዲሳተፉ ጥሪ ያቀረቡት አቶ ጌታቸው፤አቪዬሽን ባለስልጣኑ ለአልሚዎቹ ተገቢውን የቴክኒክ ድጋፍ ለማድረግ ዝግጅት ማድረጉን ገልጸዋል፡፡

የአቬየሽን ሬጉሌሽን ምክትል ዋና ዳይሬክተር ወይዘሮ ምስራቅ ጥላሁን በበኩላቸው፣ የግሉ ባለሀብትና የክልል መንግስታት በዘርፉ መሰማራታቸው ኢትዮጵያ በቀጣይ ደረጃቸውን የጠበቁ ኤርፖርቶችን ቁጥር ለማሳደግ የምታደርገው ጥረት የሚደገፍና መሰረት የሚጥል ነው፡፡ የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት ተደራሽ በማድረግ ለሀገራችን ሁለንተናዊ እድገት እና ለዜጎች ኑሮ መሻሻል የላቀ ሚና ይጫወታል ሲሉም አብራርተዋል።

በአቬዬሽን ኢንዱስትሪው የሚሰማሩ የከተማ አስተዳደሮች፣ ክልል መስተዳድሮችና የግል ባለሀብቶች ወደ ኢንቨስትመንት የሚሰማሩበት የአሰራር ማዕቀፍ መዘጋጀቱን ተናግረዋል።

ምክትል ዋና ዳይሬክተሯ፣ በአቬዬሽን የተዘጋጀው ዳይሬክቲቭ ለግል ባለሀብቶች፣ የከተማ አስተዳደሮችና ክልል መስተዳድሮች በአቪዬሽን ኢንዱስትሪው ለመሰማራት ፈቃድ ለማግኘት የሚችሉበት፣ የቴክኒክ ድጋፍ የሚደረግበት አሰራር ተዘርግቷል።

እስካሁን የአየር መሰረተ ልማትን ማስፋፋት በመንግስት ብቻ ተይዞ የቆየ መሆኑን የገለጹት ምክትል ዋና ዳይሬክተሯ፤ የግል ባለሀብቶች፤ የከተማ አስተዳደሮችና ክልል መስተዳድሮች በአነስተኛ ኤርፖርቶችና ሄሊፖርት ግንባታ መሳተፋቸው ከዚህ በፊት አገልግሎት ይሰጡ የነበሩ እንደ ደብረ ታቦር፣ ሻኪሶ፣ መካነሰላም፣ ደብረ ማርቆስና በሌሎች የአገሪቱ ክፍሎች የሚገኙ አየር ማረፊያዎችንና የመሳሰሉትን ወደ አገልግሎት እንዲመለሱ ያግዛል፡፡ ይህም የህዝብን የአየር ትራንስፖርት ጥያቄ ለመመለስ የሚያስችል ነው ብለዋል፡፡



# በቦረና ዞን በተከሰተው ድርቅ...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

604 ሺህ የሚሆኑት በመንግሥት ድጋፍ ስር የሚገኙ ሲሆን ቀሪ ከሁለት መቶ ሺህ በላይ ሰዎች ድጋፍ የሚፈልጉ መሆናቸውን ጠቁመዋል።

ከዚህ በፊት ዞኑ ዝናብ የሚያገኘው በዓመት ሁለት ጊዜ እንደነበረ ያስታወሱት የዞኑ ዋና አስተዳዳሪ፤ ባለፉት ሦስት ዓመታት ውስጥ ለተከታታይ አምስት ዙር ዝናብ ሳያገኝ መቆየቱን አንስተዋል። የተከሰተው ድርቅ በዞኑ የሚገኙትን 13 ወረዳዎች አጥቅቷል ፤ በዞኑ ከሚገኘው 60 በመቶ የሚሆነው ህብረተሰብ ድጋፍ ይፈልጋል ሲሉም ገልጸዋል።

ከችግሩ አስከፊነት አንጻር አሁን እንደ ዞን እየተሠራ ያለው ህይወት የማዳን ሥራ ነው ያሉት አቶ ጃርሶ፤ ለክልልና ለፌዴራል መንግሥት የችግሩን አስከፊነት ማሳወቃቸውን ተናግረዋል።

በዚህም መንግሥት በአንድ ዙር ብቻ ከ600 ሺህ በላይ ለሚሆኑ ሰዎች ከ90 ሺህ ስድስት መቶ ኩንታል በላይ ስንዴ፣ ሁለት ሺህ 66 ሊትር ዘይት እና 22 የውሃ ቦቲዎች እርዳታ ማቅረቡን አስረድተዋል።

በተመሳሳይ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና አጋር አካላት በድርቁ ለተጎዱ ሰዎች እርዳታ ማቅረባቸውን አሳውቀዋል።

ወደ 750 ሚሊዮን የሚጠጋ ገንዘብ እርዳታ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶችና አጋር አካላት መገኘት መቻሉንም አብራርተዋል። ነገር ግን አሁን እየተደረገ ያለው እርዳታ ለህዝቡ በቂ ስላልሆነ ለመንግሥት ማሳወቃቸውን ገልጸዋል።

በድርቁ ምክንያት ከቀያቸው የተፈናቀሉ ሰዎችን መልሶ ማቋቋም በቀጣይ የሚሰራ ስራ ነው ያሉት አስተዳዳሪው፤ እስካሁንም የመልሶ ማቋቋም ስራው ያልተሰራው ድርቁ ስላልቆመና መጀመሪያ ህይወት ማትረፍ ስለሚቀድም ነው ብለዋል።

እንደ ኃላፊው ገለጻ፤ መንግሥትም ይህን ችግር በዘላቂነት ለመፍታት የረጅምና የአጭር ጊዜ እቅድ አውጥቶ እየሰራ ይገኛል። የአካባቢው አብዛኛው ህብረተሰብ አርብቶ አደር ከመሆኑም አንጻር ያለውን የውሃ እጥረት ለመቅረፍ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት የዝናብ ውሃን መያዝ የሚችሉ 18 ግድቦችን በመገንባት ላይ ይገኛል። በተጨማሪም የከርሰ ምድር ውሃን ጥቅም ላይ ለማዋል እየተሠራ ነው።

## ኦሮሚያ ክልል

በአመልካች አድነው ጅማ እና በቤዛዊ ዳዊት መካከል ስላለው የፍትሐብሔር ክርክርን አስመልክቶ መልስ ሰጪ በክርክሩ አይነት እንዲቀርቡ እና እንዲከራከሩ ካልቀረቡ ባልቀረቡበት ቦታ ክርክሩ እንደሚካሄድ የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አሳውቋል። ቀጠሮ በ21/6/2015 ዓ.ም በ4፡00 ሰዓት ታዟል።

**የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የፍ/ብሔር ችሎት**

በአመልካች ፀሃይ ተስፋዬ እና በተጠሪ ሸዋመን ድምሩ ገዱ መካከል ስላለው የቤተሰብ ክርክር አስመልክቶ ተጠሪ ክሱን አውቆ በሸገር ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት በ27/6/2015 ዓ.ም ከቀኑ 8፡00 ሰዓት እንዲቀርብ ሲል ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የሸገር ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት የፍትሐብሔር ችሎት**

## አማራ ክልል

በአመልካች አቶ ወርቅነህ ማሞ ተጠሪ ወ/ሮ አይናዲስ ወ/አገኘ የሙብት ይለቀቅልኝ ክስ ስለአቀረበብዎ ለየካቲት 20 ቀን 2015 ዓ.ም ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት በመንዝ ጌራ ወረዳ ፍ/ቤት እንዲቀርቡና መልስዎን እንዲያቀርቡ ካልቀረቡና መልስዎን ካላቀረቡ ጉዳዩ በሌሉበት ታይቶ አስፈላጊውን ውሳኔ የሚሰጥ መሆኑ የመ/ጌ/ም/ወ/ፍ/ቤት ያስታውቃል፡፡

**በሰሜን ሸዋ ዞን የመንዝ ጌራ ምድር ወረዳ ፍ/ቤት**

## አዲስ አበባ አስተዳደር

በከሣሽ ፌ/ጠ/ዐ/ህግ እና በተከሳሽ ግብራም እንዳገር ከበደ መካከል ፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 14ኛ ወንጀል ችሎት ባለው ከተፈቀደው መጠን በላይ ጥሬ ገንዘብ ይዞ መገኘት ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ በ19/07/2015 ዓ.ም. በ4፡00 ሰዓት ላለው ቀጠሮ በችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡ ተከሳሽ በቀጣይ ቀጠሮ ባይቀርቡ በሌሉበት ፍርድ እንደሚሰጥ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

በከሣሽ ፌ/ጠ/ዐ/ህግ እና በተከሳሽ ሰጠኝ ብርሃን መኳንንት መካከል ስላለው የወንጀል ክርክር ጉዳይ ክሱን ለመስማት ለመጋቢት 12 ቀን 2015 ዓ.ም. ስለተቀጠረ ተከሳሽ ሰጠኝ ብርሃን መኳንንት በተጠቀሰው ቀን ቀጠሮ በ4፡00 ሰዓት ፌ/ከ/ፍ/ቤት ቃሊቲ ምድብ 3ኛ ወንጀል ችሎት እንዲቀርቡ ነገር ግን በተጠቀሰው ቀን ቀጠሮ ካልቀረቡ ጉዳዩ በሌሉበት እንደሚቀጥል ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአቃቂ ቃሊቲ ምድብ ችሎት**

በከሣሽ ፌ/ጠ/ዐ/ህግ እና በተከሳሽ አቶ በአካል መሣይ ግዛው መካከል በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 8ኛ ወ/ችሎት ባለው የኮንትሮባንድ ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ በ30/06/2015 ዓ.ም. በ3፡30 ሰዓት ላለው ቀጠሮ በችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡ ተከሳሽ በቀጣይ ቀጠሮ ባይቀርቡ በሌሉበት ፍርድ እንደሚሰጥ ተገልጾ የጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግላቸው ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

በከሳሽ/አመልካች ወ/ሮ የሺ መልካሙ ገ/እግዚአብሔር እና በተከሳሽ/ተጠሪ አቶ ፀጋዬ ግርማ አበራ መካከል በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 2ኛ ቤተሰብ ችሎት ባለው ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ/ተጠሪ በ22/6/2015 ዓ.ም ከጠዋቱ 3፡30 ሰዓት ላለው ቀጠሮ በችሎት እንዲቀርቡ ፍርድ ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

አመልካች ወ/ሮ ጥላዬ ሀብቶም ተጠሪ አቶ ተስፋዬ ሀይሉ ከ20/2/2000 ዓ.ም ጀምሮ የጠፉ ስለሆነ መጥፋት ውሳኔ ይሰጥልኝ ሲሉ አመልክተዋል፡፡ ስለሆነም አቶ ተስፋዬ ሀይሉ ያሉበትን የሚያውቅ ወይም ራሳቸው ካሉ ለ24/6/2015 ዓ.ም 3፡30 ሰዓት ለሆነው ቀጠሮ አ/አ/ከተማ የመ/ደ/ፍ/ ቤት ቂርቆስ ምድብ ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የቂርቆስ ምድብ ችሎት**

በአመልካች አቶ አቤል ዝና በቀለ እና በተጠሪ ወ/ሮ ምህረት ኃይሌ መካከል ስላለው የፍትሐብሔር ክርክር ጉዳዩ አመልካች አቶ አቤል ዝና በቀለ ለ27/6/2015 ዓ.ም ለሆነው ቀጠሮ ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አራዳ ምድብ 6ኛ ቤተሰብ ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

በከሳሽ/አመልካች ወ/ሮ አስናቀች ወ/ሰንበት ወ/ማርያም እና በተከሳሽ/በተጠሪ አቶ መለስ አበበ/የአያት ስም የማይታወቅ/ መካከል በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ቦሌ ምድብ 4ኛ ችሎለት ባለው ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ/ተጠሪ በ22/6/2015 ዓ.ም ከቀኑ 4፡00 ሰዓት ለስምምነት በ24/6/2015 ዓ.ም ከጠዋቱ 3፡30 ሰዓት ክስ ለመስማት ላሉት ቀጠሮዎች እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

በከሳሽ/አመልካች/ፍ/ባለመብት 1ኛ የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና በተከሳሽ/ተጠሪ ባለዕዳ 1ኛ አቶ ዘካሪያስ አላሮ ደስታ መካከል ስላለው የፍ/ብሔር ክርክር ጉዳይ ከሳሽ ፍ/ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ ተከሳሽ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ 5ኛ ባ/ኢ. ችሎት እየታየ መሆኑነ በዚህ ጋዜጣ ማስታወቂያ ጥሪ አውቀው መልሱን በጽሑፍ በ24/6/2015 ዓ.ም በ4፡00 ሰዓት በሬጀስትራር በኩል እንዲያቀርቡ እና ክስ ለመስማት 30/6/2015 ዓ.ም በ4፡00 ሰዓት ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ**

የባለንብረት ስም ኢትዮ ቴሌኮም የሠሌዳ ቁጥር ኢት 04-01-23402 የተሽከርካሪው ዓይነት ድርብ አገልግሎት የሻንሲ ቁጥር ADNCPUD22Z0053706 ሞዴል CVLULCFD22UAN-F-VH የሞተር ቁጥር YD25-628467 የሊብሬ ቁጥር 0112735 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር/ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው በ1/10/2014 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የአራዳ ቅ/ጽ/ቤት**

# ስፖርት





## በኢትዮጵያ እየተካሄደ የሚገኘው የዓለም ወጣቶች ቴኒስ ቻምፒዮና ነገ ይጠናቀቃል

**አስማረሁ ግዛው**

በኢትዮጵያ አስተናጋጅነት በአዲስ አበባ ቴኒስ ክለብ እየተካየሄደ የሚገኘው የዓለም ከ18 ዓመት በታች ቴኒስ ቻምፒዮና ነገ ፍፃሜ ያገኛል። ውድድሩ ከ28 አገራት የተውጣጡ በርካታ ተጫዋቾች ሲፎካከሩ ቆይተዋል። ቻምፒዮናው በኢትዮጵያ ሲዘጋጅ ከ17 ዓመት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲሆን፤ ላለፉት ሁለት ሳምንታት የተለያዩ የማጣሪያ፣የጥሎ ማለፍና የግማሽ ፍጻሜ ውድድሮች አስተናግዷል።

በኢትዮጵያ መዘውተር ከጀመረ ረጅም እድሜና ታሪክ እንዳለው የሚነገርለት የቴኒስ ስፖርት ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት ገደማ ተዳክሞ ቆይቷል። በአሁኑ ወቅት ግን ስፖርቱ ላይ በተሰሩት ተስፋሰጪ ስራዎች የዓለም አቀፉን የቴኒስ ፌዴሬሽን ትኩረት መሳብ በመቻሉ የአዘጋጅነቱን እድል ከ17 ዓመት በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ማምጣት እንደተቻለ ተገልጿል።

በቻምፒዮናው ኢትዮጵያን ጨምሮ ከ28 በላይ የዓለም አገራት ከተወጣጡ ከ50 በላይ ተጫዋቾችን በአራቱም የአዲስ አበባ ቴኒስ ክለብ ሜዳዎች እያፋለመ ቆይቷል። በውድድሩ 14 ኢትዮጵውያን ወጣትና ተስፈኛ የቴኒስ ተጫዋቾች የተካፈሉ ሲሆን፤ ከነዚህም ውስጥ ሶስቱ (ሁለት ወንድና አንድ ሴት) በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ አሸንፈው ነጥብ ማስመዝገብ እንደቻሉ ታውቋል። ይህም ኢትዮጵያውያኑ ተጫዋቾች ከራሽያ፣ ከአሜሪካና ፖርቹጋልን ከመሳሰሉ አገራት በቀዳሚ ስፍራ እንዲቀመጡ አድርጓቸዋል። በዚህም ውጤት ኢትዮጵያውያን ተጫዋቾች ዓለም አቀፍ ደረጃን መያዝ ስለሚችሉ በውጪ አገራት ጭምር ሄደው የመወዳደር እድል እንደሚያገኙ ታውቋል።

መሰል የውድድር አይነቶች በአገር ውስጥ መዘጋጀታቸው ለአገር ውስጥ ተጫዋቾችና ለቴኒስ ተመልካቾች ጥሩ ልምድ ከመሆኑ ባሻገር ስፖርቱ በሌላው ዓለም የደረሰበትን ደረጃ ለመከተል መልካም አጋጣሚ እንደሚሆን ተጠቁሟል።



በቻምፒዮናው 14 ኢትዮጵያውያን ወጣት የቴኒስ ተጫዋቾች ተሳትፈዋል፣

በተጨማሪም በቴኒስ ስፖርት ውስጥ ለሚሳተፉ ተጫዋቾች ፣ አሰልጣኖችና ዳኞች ልምዶችን ለመቅሰም ጥሩ እድልን የፈጠረ ውድድር መሆኑ ተገልጿል።

እንዲህ አይነት ውድድሮችን ማዘገጀት ለአገር ኢኮኖሚ አስተዋጽኦን ከማበርከት በተጨማሪ የስፖርት ቱሪዝምን በማስፋት ከዘርፉ የሚገኘውን ውጭ ምንዛሬ በማሳደግ ጥቅም እንደሚኖረው ታምኖበታል። የአገር ገጽታን በመገንባትም ፋይዳ እንዳለው ተገልጿል።

ለዚህም ተቀዛቅዞ የነበረውን የቴኒስ ስፖርትን ለማነቃቃትና አለም አቀፍ ውድድሮችን የማዘጋጀት ቁመና ላይ ለመድረስ ከሶስት ዓመታት ጀምሮ በርካታ ስራዎች መሰራታቸውን የኢትዮጵያ ቴኒስ ፌዴሬሽን ገልጿል። ፌዴሬሽኑ ለስፖርተኛው የውስጥ ውድድሮችን በማብዛት፣ አዳዲስ የአሰለጣጠን ሂደቶችን ከውጭ ባለሙያ በመጋበዝ ሲሰጥ የቆየ ሲሆን፣ ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር በመቀናጀት በመጀመሪያ ዲግሪ ለሚማሩ ተማሪዎች ስልጠና እየተሰጠ መሆኑን ገልጿል።

ስፖርቱን በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ለማስፋፋት እንዲያስችል ከኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲዎች ስፖርት ማህበር ጋር ስምምነት በመፈራረም ላለፉት ሁለት ዓመታት በሁለት ዙር ስልጠናዎችን መስጠት እንደቻለም ጠቁሟል። በዋናነት ከባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ጋር በተገባው ስምምነት መሰረት ዩኒቨርሲቲው ሰላሳ ልጆችን በባለሙያ ድጋፍ በማሰልጠን ላይ ይገኛል። በተጨማሪም ስፖርቱን ለማስፋት በቅርቡ ከአርባ ምንጭና ድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር ስምምነት ለመፈራረም ፌዴሬሽኑ በዝግጅት ላይ እንደሚገኝ አሳውቋል።

የኢትዮጵያ ቴኒስ ፌዴሬሽን ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ይልማ ከፈለኝ ለአዲስ ዘመን በሰጡት አስተያየት፤ በፌዴሬሽኑ ስር የሚዘጋጁ የአዋቂዎች ውድድር አራት መሆናቸውን ጠቁመው፤ ክለቦችና ክልሎች የራሳቸውን የውስጥ ውድድሮች እንደሚያደርጉ አስረድተዋል። በባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ከተያዙ የውድድር መርሃ ግብሮች ውጪ በቴኒስ ፌዴሬሽን የክለብ ቻምፒዮና፣ የኩነት ውድድሮችንና ሌሎች ውድድሮችን ጨምሮ በማዘጋጀት ብዙ የማበረታቻ ሽልማቶች መገኘታቸውንም ጠቁመዋል።

ከአገር ውጪ በሚደረጉ የምስራቅ አፍሪካ ዞን አምስት ውድድሮች ላይ ከ12 ዓመትና ከ14 ዓመት በታች ባሉ የዕድሜ እርከኖች እየተሳተፉ እንደሆነ የገለጹት አቶ ይልማ፤ ፌዴሬሽኑ ከ15 ዓመታት በላይ ተቋርጦ በነበረው የዴቪስ ካፕ ባለፈው ዓመት ለመጀመሪያ ጊዜ ሲካሄድ ተሳትፎ ጥሩ ውጤት እንዳስመዘገበ ገልጸዋል። በመጪው ሰኔ በሚደረገው ውድድር ላይም ለመሳተፍ በመዘጋጀት ላይ መሆናቸውን ጠቁሟል። “እንደዚህ አይነት ውድድሮች መሳተፋችን እና ቻምፒናውን ማዘጋጀታችን በጎ የሆኑ ልምዶችን እንድንቀስም ይረዳናል” በማለትም ተናግረዋል።

ስፖርቱ በባህሪው የዕድሜ ገደብ እንዳለው የገለጹት አቶ ይልማ፣ ተተኪ ላይ መስራት አማራጭ የሌለው መፍትሔ መሆኑን ተናግረዋል። ጁኒር ኢኒሼቲቭ ፕሮግራም ከዓለምአቀፉ ቴኒስ ጋር በመተባበር 14 ዓመትና ከዛ በታች ያሉ ተዳጊዎችን ብቻ መሰረት ያደረገ ስራ በጋራ እንደሚሰራም አክለዋል። ለዚህም የገንዘብ፣ የቁሳቁስና ሙያ ድጋፎችን እንደሚያገኙ ጠቁሟል። እንደ አቶ ይልማ ገለጻ፣ ሌሎች ዓለም አቀፍ ውድድሮችን በቅርቡ ወደ ኢትዮጵያ ለማምጣት ንግግሮች እየተደረጉ እንደሆነና ከተቻለ በዚህ ዓመት ካልሆነ ግን በሚቀጥለው ዓመት ለማምጣት ተስፋሰጪ ምላሽ መገኘቱን ተናግረዋል። “ውድድሩን ከማዘጋጀቱ አስቀድሞ የውድድር ቁመና ላይ ስለመገኘታችን የማዘወተሪያ ስፍራዎች መጠን አይቶ ስላጸደቁልን አሁንም ውድድሩን ለሚያዘጋጀው አካል ዕድሉ እንዲሰጠን ከመጠየቅ አንቦዝንም” ሲሉም አስረድተዋል።

የቴኒስ ስፖርት በኢትዮጵያ መዘውተር የተጀመረው በአጼ ምኒልክ ዘመነ መንግስት በፈረንሳውያን የባቡር ሃዲድ ዝርጋታ ሰራተኞች እንደሆነ መረጃዎች ይጠቁማሉ።


## የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ

ንብ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ የተበዳሪው ወይም የመያዣ ሰጪ ስም፣ የሚሸጠው ንብረት ዓይነትና የሚገኝበት ቦታ፣ አበዳሪው ቅርንጫፍ፣ የሐራጁ መነሻ ዋጋ ፣ የሐራጁ ቀንና ሰዓት ከዚህ በታች በተመለከተው መሠረት በመያዣ የያዛቸውን ንብረቶች በአዋጅ ቁጥር 97/90 እና 1147/2011 መሠረት በግልጽ ሐራጅ ስለሚሸጥ በሐራጁ መሳተፍ የሚፈልግ የግምቱን 1/4ኛ በሲፒኦ፣ በባንክ በተረጋገጠ ቼክ ወይም በጥሬ ገንዘብ በማስያዝ በሐራጁ ቀን፣ ሰዓትና ቦታ በመገኘት መሳተፍ የሚችል ሲሆን የሐራጁ አሸናፊዎች ያሸነፉበትን ገንዘብ በ15 ቀናት ውስጥ አጠናቅቀው መክፈል ሲኖርባቸው ካልከፈሉ ጨረታው ተሰርዞ ያስያዙት ገንዘብ አይመለስም፡፡ ባንኩ የተሻለ መንገድ ካገኘ ሐራጁን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሠረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡ ስለንብረቱ መረጃ ማግኘት የሚፈልግ አበዳሪ ቅርንጫፉን ማነጋገር ይችላል፡፡ ሻጭ ባንክ ስመንብረቱ ለገዥው እንዲዛወር ለሚመለከተው የመንግስት አካል ተገቢውን የድጋፍ ደብዳቤ ይጽፋል፡፡ ገዥ ከስም ማዛወር ጋር በተያያዘ ሊከፈሉ የሚገባቸው የመንግስት ታክሶች፣ የካፒታል ዕድገት ታክስ እና ተጨማሪ እሴት ታክስን ጨምሮ የመክፈል የሕግ ግዴታ አለበት፡፡ በሐራጁ ላይ ተበዳሪ/ መያዣ ሰጪ ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው መገኘት የሚችሉ ሲሆን፣ ባይገኙ ሂደቱ የሚቀጥል ይሆናል፡፡

| ተ.ቁ | የተበዳሪው/የመያዣ ሰጪ ስም | አበዳሪው ቅርንጫፍ | የሚሸጠው ንብረት ዓይነትና የሚገኝበት ቦታ | የሐራጁ መነሻ ዋጋ በብር | የሐራጁ ቀንና ሰዓት |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | አቶ አዳነ ግርማ | ሀዋሳ ዋርካ | በስማቸው የተመዘገበ ሀዋሳ ከተማ ምሥራቅ ክ/ከተማ ውስጥ የሚገኝ 200 ሜ/ካሬ ይዞታ ያለው ባለ ሁለት ወለል የንግድ ህንፃ፣ | 3,000,000.00 | 19/07/2015 ከ4፡00-6፡00 ሰዓት |
| 2. | አቶ ተካ ሻፊ ያሲን/ወ/ሮ ሽባወርቅ ዳለቻ መኣኔ | ራጉኤል | በወ/ሮ ሽባወርቅ ዳለቻ መኣኔ ስም የተመዘገበ አዲስ አበባ ከተማ ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ ወረዳ 3 ጀሞ አንድ ኮንዶሚኒየም ውስጥ የሚገኝ 42 ሜ/ካሬ ይዞታ ያለው የኮንዶሚኒየም መኖሪያ ቤት | 1,000,000.00 | 19/07/2015 ከ4፡00-6፡00 ሰዓት |
| 3. | አቶ አብይ ምትኩ እጅጉ | ዐብይ ቅርንጫፍ | በስማቸው የተመዘገበ አዲስ አበባ ንፋስስልክ ላፊቶ ክ/ከተማ ወረዳ 01 ውስጥ ጀሞ ሳይት የሚገኝ 45 ሜ/ካሬ ይዞታ ያለው የኮንዶሚኒየም መኖሪያ ቤት፣ | 2,000,000.00 | 20/07/2015 ከ4፡00-6፡00 ሰዓት |
| 4. | አቶ ገ/እግዚአብሔር ኪዳኔ ተክሌ | አዲሱ ገበያ | በአቶ ገ/እግዚአብሔር ኪዳኔ ስም የተመዘገበ የሠሌዳ ቁጥር 3-71586 ኢት የሆነ ሲኖ ትራክ የጭነት መኪና አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ በሚድክ ኮንስትራክሽን እና ሸገር ዳቦ መካከል በሚገኘው መንገድ ወደ ውስጥ 200 ሜ/ገባ ብሎ ከሚገኘው ጎህ አውቶሞቲቭ የመኪና ማቆሚያ ቆሞ የሚገኝ | 2,600,000.00 | 07/07/2015 ከ4፡00-6፡00 ሰዓት |
| 5. | ሲስቴክ ሶሉሽን ኃላ/የተ/የግ/ማህበር/አቶ ጥላዬ ጨዋቃ | ፍላሚንጎ | በአቶ ጥላዬ ጨዋቃ ስም የተመዘገበ አዲስ አበባ ከተማ ኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከተማ ወረዳ 05 ውስጥ የሚገኝ 239 ሜ/ካሬ ይዞታ ያለው መኖሪያ ቤት፣ | 6,500,000.00 | 21/07/2015 ከ4፡00-6፡00 ሰዓት |
| 6 | ወ/ሮ አያንቱ ከበደ ኦብሳ | ንብ ፕሪሚየም | በስማቸው ተመዝግቦ የሚገኝ የሠሌዳ ቁጥር 3-B44737 ሱዚኪ ዲዛየር አውቶሞቢል መኪና ሰንጋ ተራ ኮሜርስ/ት/ቤት ፊት ለፊት ከሚገኘው ከንብ ባንክ ዋና መሥሪያ ቤት ህንፃ B-4 ቆሞ የሚገኝ፣ | 1,150,000.00 | 08/07/2015 ከ4፡00-6፡00 ሰዓት |
| 7 | አቶ ሙሉነህ ገላና/አቶ ግርማ ጭንድ | ዳርጌ | በአቶ ግርማ ጭንድ ስም የተመዘገበ አመያ ወረዳ ጊንዶ ከተማ ውስጥ የሚገኝ 200 ሜ/ካሬ ይዞ ያለው መኖሪያ ቤት፣ | 350,000,.00 | 22/07/2015 ከ4፡00-6፡00 ሰዓት |
| 8 | አቶ ታከለ ዋቸሞ | ወላይታ ሶዶ | በስማቸው የተመዘገበ ቦዲቲ ከተማ ሀጋዝ ቀበሌ ውስጥ የሚገኝ 500 ሜ/ካሬ ይዞታ ያለው የንግድ ቤት | 750,000,.00 | 20/07/2015 ከ4፡00-6፡00 ሰዓት |
| ድጋሚ የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ | | | | | |
| 1 | አቶ አብርሃም ጫሚሶ ዲዶ | ሀደሮ | በስማቸው የተመዘገበ ሀደሮ ከተማ ውስጥ የሚገኝ 552 ሜ/ካሬ ይዞታ ያለው መኖሪያ ቤት፣ | 750,000,.00 | 21/07/2015 ከ4፡00-6፡00 ሰዓት |

## ንብ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ